# "የጥምቀት ተመላሾች" ማንነት እና የጥቅሶቻቸው ዐውዳዊ ፍካሬ

ገዛኸኝ ጸጋው[1]

**አጠቃሎ**

ይህ የፎክሎር ጥናት÷ የጥምቀት ሥራተ እምነት (ritual)፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ ዋና ዋና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት መካከል አንዱ እንደሆነ፣ በሀገሪቱ መከበር ከጀመረም እጅግ በርካታ ዓመታትን እንዳስቆጠረና በየዘመናቱ የተለያዩ ለውጦችን እያስተናገደ እዚህ እንደደረሰ ተቃኝቷል፡፡ በተለይም ከአዲሱ ሚሊኒየም ዋዜማ ጀምሮ በሥራተ እምነቱ ላይ አዳዲስ ለውጦች ሲከሰቱበትና ወጣት "የጥምቀት ተመላሾች"[2] አዳዲስና ያልተለመዱ ሁነቶች ሲከውኑ መታየቱ፣ ጥናቱ ትኩረቱን በነዚሁ አዳዲስ ሁነቶች ላይ እንዲያደርግ የመነሻ ምክንያት ሁነውታል፡፡ ጥናቱ፣ የጥምቀት ተመላሾቹን ማንነት እና የጥቅሶቻቸውን ምንነት፣ ከሀገሪቱ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች እና/ወይም ማኅበረ ባህላዊና ታሪካዊ ዐውዶች ጋራ እያናበቡ መተንተንና መፈከር ዋና ዓላማ ሲሆን፣ ወጣቶቹ እንዴት ሊደራጁ ቻሉ? ይህን ዓይነቱን አገልግሎት የመረጡት ለምንድን ነው? የገንዘብ ምንጫቸው ምንና ማን ነው? ወጣቶቹ ለበዓሉ በሚያዘጋጇቸው አልባሳትና "ባነሮች" ላይ የሚያሳትሟቸው ጥቅሶች ምንድን ናቸው? የጥቅሶቹ አንድምታ ምንድን ነው? ወዘተ. ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡ ጥናቱ፣ ዓይነታዊ የምርምር ፈለግን የተከተለ በመሆኑ፡- በምልከታ፣ በኢ-መደበኛ ቃለመጠይቅና በጽሑፍ ሰነዶች ምርመራ አማካይነት፣ ቀዳማይና ካልዓይ መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ አጥኚው፣ የተጠናቀሩትን መረጃዎች በዓውዳዊ ፈለግ ማንጸሪያነት በመተንተንም፣ ጥቅሶቹ ለወጣቶቹ የታመቀ የውስጥ ብሶት መተንፈሻ፣ የትግል መሣሪያቸው እንደሆኑ አመላክቷል፡፡ የጥናት ግኝቱን መሠረት በማድረግም፣ ‹በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በየዘመናቱ መንግሥታት አዳዲስ የፎክሎር ዘውጎች እንዲፈጠሩ ምክንያት ይሆናሉ ማለት ነው?› የሚል የምርምር ጥያቄ ማርቀቅ እንደሚቻል ይጠቁሟል፡፡

---

[1] ገዛኸኝ ጸጋው (ፒኤችዲ.) የሥነ ጽሑፍና ፎክሎር መምህር ÷ በኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር የ***ብሌን*** (የሥነ ጽሑፍና ፎክሎር መጽሔት) ማኔጂንግ ኤዲተር፡፡

[2] ቀደም ሲል ባልተለመደ መልኩ፤ በየሰፈሩ ለክብረ በዓሉ ድምቀት አካባቢያቸውን፣ የታቦት መሄጃ መንገዶችን በማስዋብ፣ ድንኳን በመትከል፣ መድረኮችን በመሥራት፣ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ሠንደቅ ዓላማዎችን በመስቀል፣ የታቦት መሄጃ ረጃጅም ቀያይ ምንጣፎችን በመዘርጋት፣ የክብረ በዓሉን ተሳታፊ ሕዝብ በጉልበት/በኃይል "ሥርዓት በማሲያዝ" ወዘተ. የተለያዩ ተግባራትን የሚወጡ፣ የጥምቀት ሥራተ እምነቶች ላይ የሚሳተፉ ወጣቶችን ብቻ ይመለከታል፡፡ የምርምሩ ተሳታፊ የቤተ ክርስቲያኗ ሊቃውንት፡- "የጥምቀት ተመላሾች" ፣ "መጥምቃውያን" አንዳንድ ጊዜ ደግሞ "ቁጡ ሐዋሪያ" እንደሚሏቸው ገልጸዋል፡፡ ጥናቱ ግን በጥምቀት በዓል ላይ ስለሚያተኩር፣ በብዙዎች የሚዘወተረውን ስያሜ ["የጥምቀት ተመላሾች"ን] ተጠቅሟል (ዝርዝሩ በሚቀጥለው የጥናቱ ክፍል ይመለከቷል)፡፡

## 1. መግቢያ[3]

በድምቀት ከሚከበሩት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት መካከል አንዱ የሆነው የጥምቀት ሥራተ እምነት[4] (ritual)፤ በኢትዮጵያ መከበር ከጀመረ ከ1ሺህ 7መቶ ዓመታት በላይ እንደተቆጠሩ ይነገራል። በርግጥ፣ "የንግሥት ህንደኬ የግምጃ ቤት ሹም የነበረው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ (ሕፅው) ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ፣ ፊልጶስ በተባለ ካህን በ 34 ዓ.ም. በመጠመቅ" ቀዳሚዉ እንደሆነ አንዳንድ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ (በላይ 1995፡ 28-29)፡፡ የጥምቀት ሥራተ እምነት በኢትዮጵያ በወጉ የተጀመረውና እየተስፋፋ የሄደው ግን፣ ከእነ አብርሃ አጽብሃ የንግሥና ዘመን ከ 330 ዓ.ም. ጀምሮ እንደሆነ የቤተ ክርስቲያኗ የጽሑፍ ሠነዶች ይጠቁማሉ (ኢኦተቤ. 2000፡16፤ አባ ጎርጎርዮስ 1994፡18)፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጥምቀት ከመቼ ጀምሮ መከበር እንደጀመረ ከመላምት የዘለለ ጥልቅ ሳይንሳዊ ጥናት የተደረገበት ማስረጃ እስከ አሁን የተገኘ አይመስልምና ወደፊት ጥልቅ ጥናት እንዲደረግበት ይመከራል።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክብረ በዓሉ በተለያዩ ማኅበረ ፖለቲካዊ ዐውድ ውስጥ ሲያልፍ ብዙ ለውጦች እያሳየ እዚህ እንደ ደረሰ በጥምቀት በዓል ምንነት እና በማኅበረ ባህላዊ ዐውዶቹ ፋይዳ ላይ ያተኮረው፣ የአበባው (እኤአ. 2006) ጥናት ያትታል። በኢትዮጵያ "አብዮትና ሃይማኖት" ላይ ምርምር ያደረጉት ኤዲ (Eide 2000: 249፤ ከዚህ በላይ በእንግሊዘኛ በቀጥታ በቀረበ ጥቅሳቸው) ደግሞ፣ "ሃይማኖታዊ ሥራተ እምነቶችና ሂደቶቻቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አሁንም ድረስ፣ ትርጉም ያለው ሚና እየተጫወቱ ነው፤ የኢትዮጵን ኅብረተሰብ ተለዋዋጭና ዝንቅነት ለመገንዘብ የሃይማኖት ጥናት ጠቃሚ ነው" ብለዋል፡፡ እንደ ሁለቱ ምርምሮቹ ዕይታ ከሆነ፣ ‹በጥምቀት ሥራተ እምነት ላይ የሚታየው ለውጥ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የሀገራዊ ለውጥ ማሳያ፣ የመንግሥታዊ ሥርዐቱ ማንጸሪያ መሆኑ አይቀርም› ብሎ ማተት ይቻላል (Orlowska 2009, Chaillot 2002)፡፡

እስከ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በዘለቀው በረጅሙ የሰሎሞን ሥርወ መንግሥት ውስጥ አስተዳደራዊ ሚና ከነበራት እና ፊደል ቀርጻ በሀገር በቀል ዕውቀት የዳበረ ሥርዓተ ትምህርት እየሰጠች፣ የሀገር ባለውለታነቷን ያጸናች ቤተ ክርስቲያን[5] (የሃይማኖት ተቋም) አካል የሆነ

---

[3] የዚህ ጥናት መነሻ፣ "Advanced Methods in Folklore (Folk-805)" ለተባለ ለ3ኛ ዲግሪ የድኅረ ምረቃ ትምህርት ኮርስ ማሟያ የተሠጠ የቤት ሥራ ሲሆን፤ አጥኚው፣ የወቅቱን ትኩሳት እንደ ቴርሞ ሜትር ለመለካት የሚያግዙ ያላቸውን ፎክሎሮች ከነማኅበረ ባህላዊ ዐውዶቻቸው እንዲሰንድ ምክንያትና ብርታት የሆኑትን ዶ/ር ፈቃደ አዘዘን ያመሰግናል፡፡

[4] የአብዛኞቹ ሙያዊ ቃላት ፍቾች የተወሰዱት፣ "የፎክሎር መዝገበ ቃላት ጥንቀራ ቅድመ ዝግጅት" ከሚለው ከሰይፉ መታፈሪያ የምርምር ጽሑፍ ነው (*የኢትዮጵያ ጥናት መጽሔት*፡ ቅጽ 26፡ ቁጥር 1 ጁን 1993፤ ገጽ 73-116)፡፡

[5] በርግጥ፣ "የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሀገር በቀል ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ በመስኩ ሊቃውንት የሚነገርለት የወሎዉ "ሐይቅ እስጢፋኖስ" ገዳም ባለቤት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ ሥርዓተ ትምህርቷ ከ8ቱ የዓለማችን ታላላቅ የሰው ልጅ ሥልጣኔዎች መካከል አንዱ እንደሆነና ከኢትዮጵያም አልፎ የአፍሪካ ብቸኛ የሥልጣኔ ምልክት እንደሆነ የተለያዩ ተመራማሪዎች አየተናገሩ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ሳሙኤል ሐንቲግተን (Huntington 1996፡47) The *Clash of Civilizations and the Remaking of World Order* በሚለው አነጋጋሪ መጽሐፋቸው ላይ፣ "Most major scholars of civilization except Braudel do not

የጥምቀት ሥራተ እምነት፣ በየዘመኑ የነበሩ ነገሥታት የአስተሳሰብና የአሠራር አሻራቸውን ሊያሳርፉበት እንደሚችሉ ይጠበቃል (ገዛኸኝ 2009)፡፡ እንደውም፣ ጥምቀት አሁን ባለው ይዘትና ቅርጹ በኢትዮጵያ ብቻ እንደሚከበር አበባው (2006፡170) Berg (1999) ጠቅሰው ማስረገጣቸውን ያገናዝቧል።

እዚህ ላይ፣ የጥምቀት ክብረ በዓል፣ በዓለም ላይ እንደ ሌሎች ሀገራት ሳይጠፋ፣ በኢትዮጵያ በተለየ መንገድ እንዲከበርና እንዲዘልቅ ያደረገው፣ በየጊዜው የተነሱት ነገሥታት የሚያረቁት ሥርዓተ ድንጋጌ (አዋጅ) ይሆን? የሚል ጥያቄ ሊያጭርብን ይቻላል። እንደተባለውም፣ የጥምቀት በዓል በ4ኛው ክ/ዘመን ላይ ዕለቱ ጥር 11 ታስቦ ቢከበርም፣ "በዓለ ጥምቀትን አሁን ባለው መልኩ በሜዳ ላይና በውሃ አካላት ዳር ማክበር የተጀመረው" ግን ከ6ኛ ክ/ዘመን ጀምሮ ነበር (አበባው 2006፡158)፡፡ በ12ኛ ክ/ዘመን ንጉሥ ላሊበላ ("ላል ይበላ") በአንድ አካባቢ የሚገኙ ቤተ ክርስቲያኖች በአንድ ላይ ሰብሰብና ደመቅ ብለው፣ እንዲያከብሩ አዘዙ-ሥርዓት ደነገጉ፡፡ በ14ኛው ክ/ዘመን አፄ ዘርዐ ያዕቆብም፣ ጥር 10 ታቦቱ ወንዝ ወዳለበት ስፍራ ሂዶ እንዲያድር በሰጡት ትዕዛዝ መሠረት፣ ቀኑ የከተራ ሥራተ እምነት ማስፈጸሚያ ሆኖ መከበር ጀመረ፡፡

አፄ ናዖድ ደግሞ፣ "ማንኛውም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ምዕመን ታቦተ ሕጉ ወደ ባሕረ ጥምቀቱ በሚወርድበት" (አበባው 2006፡164) እና ወደ ቤተ መቅደሱ በሚመለስበት ጊዜ፣ አጅቦ ማድረስ እንዳለበት አዋጅ በማስነገራቸው፣ ዛሬ በጃን ሜዳ ("ጃንኾይ ሜዳ") በርካታ ታቦታትና ካህናት፣ በመቶ ሺዎች በሚቆጠሩ ምዕመናንና የበዓሉ ተሳታፊዎች ታጅበው አንድ ላይ እንዲገኙ ምክንያት ሆነዋል (በላይ 1995፤ አባ ጎርጎርዮስ 1994)። በመሆኑም ጥምቀት፣ ከአንድ የሃይማኖት ተቋም መገለጫነት ባለፈ ሀገራዊ መለዮ እስከመሆን መድረሱ፣ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ፎክሎራዊ ዝንቅነቱን ያጎላለት[6] ይመስላል፡፡

ከዚህ ጥቅል የማኅበረ ባህላዊ ወታሪካዊ ዐውዶች ማሕቀፍ ውስጥ ሳንወጣ፣ ከአዲሱ ፪ሺኛ ዓመት (ሚሌኒየም) መባቻ ጀምሮ፣ በጥምቀት ሥራተ እምነት ላይ የሚታዩ አዳዲስ የሥራተ እምነት ክዋኔዎች እየተከሰቱ እንደነበረ ይነገራል፡፡ ሥራተ እምነቶችም (rituals) በባህርያቸው፣ ተለዋዋጭ መሆናቸው ይታወቃል (Bell 1997)፡፡ በርግጥም፣ በክብረ በዓሉ ላይ በተለይ

---

recognize a distinct African civilization. … Historically, Ethiopia constituted a civilization of its own" ካሉ በኋላ እንደገና፣ "Ethiopia, for example, is culturally isolated by its predominant language, Amharic, written in the Ethiopic script; its predominant religion, Coptic Orthodoxy; its imperial history" (1996፡136) በማለት በምሳሌ አስደግፈው ማብራራታቸውን ይጠቅሷል፡፡ ዶናልድ ሌቪን (Levine 2006፡12) በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ ቅዱሳት መጻሕፍቷና የነባሩ ሥርዓተ ትምህርቷ አካል የሆነ የቅኔ ቤት ዕውቀቷ ከ6ቱ የዓለማችን ታላላቅ የሰው ልጅ ሥልጣኔዎች መካከል አንዱ መሆኑን መስክረዋል፡፡

[6] ይኸውም፣ የተለያዩ ሀገረሰባዊ ተረኮች (folk narratives) እና/ወይም ሀገራዊ ርዕዮተ ዓለሞች (ideologies) በአንድ በኩል እንዲሁም፣ ተደጋግመው በመከወን ፈር የያዙ የሕይወት ልምዶች እና/ወይም ትውፊቶች (traditions) በሌላ በኩል እንደሆኑ፤ አንዳንድ ጊዜ ተነጣጥለው፣ ብዙ ጊዜ ግን ተካልሰው የሚቀነቀኑበት ማኅበረ ባህላዊ እሴትነቱን ያፀናለት ይመስላል ለማለት ነው።

የወጣቶች እንቅስቃሴ፣ ከሃይማኖታዊ ተቋሚ ትይዩ በተመሳሰሎና በታቅርኖ የቆሙ የሚያስመስሏቸው ያልተለመዱ አዳዲስ ሁነቶችን ሲከውኑ ታይተዋል።

ታዲያ፣ ያልተለመዱ አዳዲስ ሥራተ እምነቶችን የሚከውኑት እነዚህ ወጣቶች ("የጥምቀት ተመላሾች") እነማን ናቸው? "ለመሆኑ ማን ለዚህ አገልግሎት መረጣቸው? እንዴት ሊሰበሰቡ ቻሉ? ይህኛውን ዓይነት አገልግሎት ለምን መረጡት? የገንዘብ ምንጫቸው ከየት ነው? እንዴት እንደ አሸን በአንድ ጊዜ በሁሉም የሀገሪቱ ቦታዎች ሊፈሉ ቻሉ?" ለበዓሉ ባዘጋጇቸው አልባሳቶችና "ባነሮች" ላይ የሚያሳትሟቸው ጥቅሶች ምንድን ናቸው? ለምንና እንዴት ይገለገሉባቸዋል? የሚሉትን ጥያቄዎች መንግሥትን ጨምሮ ብዙዎች ያነሷቸዋል (ዳንኤል 2003፡ 1)፡፡ አጥኚው፣ ለጥያቄዎቹ ምልሽ በሚሰጥ መልኩ፣ በፎክሎር ሙያ ማንጸሪያነት የተሠራ አንድም ጥናት ሊያጋጥመው አለመቻሉ፣ ለዚህ ጥናት መነሻና ማትጊያ ሆኖታል፡፡ ስለዚህ ጥናቱ፣ ከላይ የቀረቡትን ዝርዝር ጥያቄዎች፣ በሁለት መሠረታዊ መሪ ጥያቄዎች ማሕቀፍ ቀንብቦ ምላሽ እንደሚሰጥ ይታመናል፡፡ የጥምቀት  ተመላሾች ማንነት እና የጥቅሶቻቸውን ምንነት፣ ከሀገሪቱ የጊዜዉ ሁኔታዎች (ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች) እና/ወይም ማኅበረ ባህላዊ ወታሪካዊ ዐውዶች ጋራ እያናበቡ መተንተንና መፈከር፣ የጥናቱ ዋና ዓላማዎች ናቸው፡፡

## 2. የጥናቱ ዘዴ እና ማንጸሪያዎቹ

ይህ ጥናት፣ በማኅበረ ባሕላዊ ዐውድ ውስጥ የሚከወን የፎክሎር ጥናት በመሆኑ፣ የዓይነታዊ ምርምር ፈለግን (qualitative research approach) የተከተለ ሲሆን፣ የተለመዱትን ሁለት ዓይነት የመረጃ ምንጮች ተጠቅሟል፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮችን በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታና በኢመደበኛ ቃለመጠይቅ እንዲሁም፣ ካዕላይ የመረጃ ምንጮች የተለያዩ የታተሙና ያልታተሙ የጽሑፍ ሰነዶችን በመፈተሽ ለማሰባሰብ ጥረት አድርጓል።

ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው የምርምሩ ተሳታፊዎች፣ በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ብዙ አሀዶችን[7] ያበረከቱ፣ በተለይ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ላይ ጥልቅ ዕውቀትና የሕይወት ልምድ አላቸው ተብለው በአጥኚው የታመነባቸው፥ ስለ ቤተ ክርስቲያኗም፣ ቤተ ክርስቲያኗንም ጠንቅቀው የሚያውቁና የሚታወቁ[8] የቅርብ አገልጋይ ዲያቆናት ናቸው፡፡     ከጥር 7 እስከ ጥር 12፣ 2004 ዓ.ም. ባሉት ቀናት በጃን ሜዳና በዙሪያው ባሉ ሠፈሮች (ከአራት ኪሎ እስከ ቤላ) የጥምቀት ተመላሾቹ፣ ከከተራ በዓሉ ዋዜማ ቀደም ብለው በየአካባቢያቸው (በየማኅበራዊ ቡድናቸው) ካደርጉት ዝግጅት ጀምሮ፣ በበዓላቱ ቀናት የነበራቸውን ተሳትፎና አጠቃላይ

---

[7] አሀድን ("text") ከፎክሎር ጽንስ ሐሳብ አንፃር ለማጤን የቃሉን መነሻ ምንጭ ወይም ሥርወ ቃል ማወቅ ይመከራል፡፡ "text" የሚለው ቃል ምንጩ "texere" የሚለው የላቲን ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም፣ "to weave" ("መሸመን" ፤ "ማደወር" ወይም "ማድራት") ማለት እንደሆነ Sims and Stephens (2005፡19) ያስረዳሉ፡፡ አሀድ ሥርወ ቃሉ ከጽሑፋዊ ፅንሰ ሐሳብነቱ ባሻገር፤ "ቃላትን" ፤ "ሐሳብን" ፤ "ባህርይን" እና "ቁሳዊ ነገሮችን" እንደሚወክል ልብ ይሏል፡፡

[8] ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፣ ዲያቆን ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል እና ዲያቆን ታደሰ ወርቁ ሲሆኑ፣ ቃለ መጠይቆቹ የተደረጉት በታህሳስና በጥር፣ 2004 ዓ.ም. ነው (ዝርዝሮቹን በሚቀጥሉት ክፍሎች ይመልከቱ)።

እንቅስቃሴ የሚወክሉ መረጃዎችና ማስረጃዎች ተገኝተዋል፡፡ አጥኚው፣ ከጥምቀት ወጣቶቹ ጋራ ሙሉ በሙሉና በከፊል እየተሳተፈ[9] አልፎ አልፎ ደግሞ፣ ዳር ሆኖ አጥኚ ሳይመስል ከበዓሉ ታዳሚዎች ጋራ እየተጨዋወተ፣ በምልከታና በኢመደበኛ ቃለ መጠይቅ መረጃዎቹን ሰብስቧል፡፡ ጥናቱ፣ የጥምቀት ክብረ በዓል ያገናኟቸው ሀገረሰባዊ ቡድኖች[10] (የጥምቀት ተመላሾቹ ስብስብ) የተፈጠሩበትን አጠቃላይ ማኅበረ ባህላዊ ዐውድ እና/ወይም ከዋኔ[11] (Performance) መተንተንና መፈከር ላይ ስለሚያተኩር፣ የሚከተለው የአጠናን ዘዴ የተጠኞቹን ተለዋዋጭነትና በይነ ዲሲፕሊናዊ ተፈጥሮ ግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ይመከራል (Ben-Amos 2011, Bauman 1986)፡፡ ለዚህ ደግሞ፣ ዐውዳዊ ፊለግን[12] ማንጸሪያ (perspective) ማድረግ ተመራጭ ሆኖ ተገኝቷል፤ የዐውዳዊነት ፊለግ መሠረቱ የዐውድ ግንዛቤ ነውና፡፡ከመነሻው የጥምቀት ተመላሾች ወደ ጥምቀት መድረክ የመጡበት ገፊ ምክንያት በራሡ፣ በተለያዩ ጊዜና ቦታ የተከወኑ ውስብስብና ንጥልጣይ ሁነቶች ያዋቀሩት ሀገራዊ ዐውድ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ዐውዱ፣ ማኅበረ ባህላዊ ወታሪካዊ ዳራዎችን ያቀፈ፣ የተለያዩ ማንጸሪያዎች ያሏቸው ሌሎች የዐውድ ዓይነቶችን የሚያጠቅስ፣ በአንጻራዊነት ሰፋ ያለ ፅንሰ ሐሳባዊ ማሕቀፍ ነው፡፡ የጥምቀት ተመላሾቹ በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የተለያዩ ጥቅሶችን የሚከውኑበት ሁኔታ፣ ሁኔታዊ ዐውዱ፣ በስሱ እንኳን ከገፉትና ካሰፉት ሌላኛው ማኅበረ ፖለቲካዊ ዐውድ ሲሆን፣ ከክብረ በዓሉ ውጭ ያሉ ሌሎች ሁኔታዎችን ሁሉ ማካተቱ ይታወቃል።

ጥቅሶቹን የጥምቀት ተመላሾች በሚከውኗቸው፣ በሚያልሟቸው፣ በሚበይኗቸውና በሚያብራሯቸው መንገድ፣ አጥኚው ይገነዘባቸው፣ ይበይናቸው፣ ያብራራቸውና ይፈክራቸው ዘንድ፣ ቦማን (Bauman 1986, 1977) የከዋኔን ንድፈ ሐሳብ ሲያቀነቅኑ ትኩረት ያደረጉባቸውን 6 የዐውድ ዓይነቶች (ትርጓማዊ፣ ተቋማዊ፣ ተግባቦታዊ፣ ማኅበረሰባዊ፣ ግለሰባዊ[13] እና ሁኔታዊ ዐውዶች) በማንጸሪያነት ተጠቅሟል፡፡ ጥቅሶቹ፣ በእነዚህ በ 6ቱ ዐውዶች ውስጥ ህልውናቸውን

[9] አጥኚው፣ ሙርቺሰን (Murchison 2010፡84) የዘረዘሯቸው የምልከታ ዘዴ አማራጮችን ሁሉ ቢጠቀምም፣ አብዛኛውን ምልከታ ያካሄደው ግን በከፊል ተሳትፎ ነበረ፡፡

[10] የተለያዩ የሀገረሰባዊ ቡድን የመመደቢያ መንገዶች ስለመኖራቸው ያተቱት ሹሜከር (Schoemaker 1990፡ 4)፣ Stahl ን (1989፡ 35) ጠቅሰው፣ ስምንት የምደባ መንገዶችን ዘርዝረዋል፡፡ ምደባዎቹም፡- ጾታ/ሥራተ ጾታ፣ ቤተሰብ፣ ሥራ፣ ማኅበራዊ ኔትዎርክ (የመደብ ዝምድና)፣ የዕድሜ ደረጃ፣ ሃይማኖት፣ ቦታ (አካባቢ) እና ብሔረሰብ በማለት በቅደም ተከተል አስቀምጠዋል፡፡ ስለዚህ የጥምቀት ተመላሾቹ ሀገረሰባዊ ቡድን፣ በዋናነት የጥምቀት ክብረ በዓል ላይ "የሚያስፈልጉ" ተግባራት መከወን (ለምሳሌ የሥራት እምነቱ ማድመቂያ የሚሆኑ፣ በአልባሳትና በባነሮች ላይ የሚታተሙ ሃይማኖታዊ ጥቅሶችን ማዘጋጀት) ማዕከል አድርጎ የተመሠረተ በመሆኑ፣ በ "ሥራ" ምድብ ውስጥ ይዋገናል፡፡ ቡድኑን፣ በሌላ ሰፊ ዐውድ ማንጸሪያነት ማየት ከተፈለገም፣ "ሃይማኖት" ምድብ ውስጥ ሊዋገን ይችላል ማለት ነው፡፡

[11] ጥናቱ፣ ሁለቱን ቃላት በማተካከት የተጠቀመው እነ ጀሰን (Jason 1997፡ 221) "In recent decades, in folkloric parlance, ‹context› has been narrowed down to ‹performance,› ie..." ስለሚሉ ነው፡፡

[12] Toelken (1996፡5) የተባሉ የአሜሪካ ፎክሎር ተመራማሪ፣ "Probably the most prominent approach to folklore in recent years has been *contextual*" በማለት አውዳዊ ፊለግ፣ ከሁሉም የተሻለ ተመራጭና ዘመነኛ ፊለግ ስለ መሆኑ ያተቱትን፣ እዚህ ላይ ቢታወስ መልካም ነው፡፡

[13] ግለሰባዊ ዐውድ፣ Oring (1986፡135-141) የተለያዩ የፎክሎር ዘውጎችን ለመዳኘትና ለማስተንተን ይበጃሉ ካሏቸው 4 የዐውድ ዓነቶች (ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ግለሰባዊ እና ንጽጽራዊ) መካከል አንዱ ሲሆን፣ ወጣቶቹ የተለያዩ የጥምቀት ሥራተ እምነቶችን ሲከወኑ፣ ከእያንዳንዱ ሀገረሰባዊ ቡድን ወይም ከአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት ግለሰባዊ ሕይወት ጋራ ያላቸውን ዝምድና ለመመርመር ያስችላል፡፡

እንደመሠረቱና በእነሱ ውስጥ ሊጠኑ እንደሚገባ አጥኚው ያምናል (ዝርዝሩን፣ ይበልጥ ጥቅሶች በተፈከሩበት ክፍል ይመልከቱ)፡፡

### 3. የጥምቀት ተመላሾቹ ማንነት፣ ማኅበረ ባህላዊ ዳራቸው

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፣ "የዳንኤል እይታዎች" በሚለው ጦማራቸው (Blog) ጥር 12 ቀን፣ 2003 ዓ.ም. "የጥምቀት ተመላሾች" በሚል ርዕስ በጥምቀት በዓል ላይ በድንገት ስለተከሰቱ ወጣቶች አንድ ጽሑፍ አስነብበዋል። ጽሑፉ፣ የወጣቶቹን እንቅስቃሴ እንደሚከተለው ይገልጻል፤

> ከኮተቤ አዲሱ መንገድ እስከ ሲኤምሴ መንገድ ያለው ፒስታ መንገድ ቀኑን ሙሉ ውሃ ሲጠጣ ነበር። መቼም ይህ መንገድ እንደዛሬ አልፎለት አያውቅም። ሰማዩ ደግሞ በአረንጓዴ እና ቢጫ ቀይ ባንዲራ አጊጧል። ከመንገዱ ግራ እና ቀኝ ያለው ሳር ታጭዶ የቼልሲን ስታዲዮም መስሏል። አስር ሰዓት ተኩል ሲሆን ሕዝቡ እንደጎርፍ እየፈሰሰ መጣ። ነጭ ጎርፍ ታውቃለችሁ .... ግራ እና ቀኝ በቢጫ ቀዩ ከናቴራ የተዋቡ ሴቶች እና ወንዶች ወጣቶች መንገዱን እጅ ለእጅ ተያይዘው አጥረውታል... አንድ ሃያ ወጣቶች ወደ አምስት መቶ ሜትር ምንጣፍ እየዘረጉ ከታቦቱ ፊት ፊት ያነጥፋሉ። ከኋላ በኩል ደግሞ ሌሎች ወጣቶች ታቦቱን የያዙት ካህናት ያልፉበትን ምንጣፍ ይጠቀልላሉ...(ገጽ 1)

አብዛኞቹ ወጣቶች፣ "ፀጉራቸው የተቆጣጠረ፤ እንደ አፄ ቴዎድሮስ ፀጉራቸውን የተሡሩ፤ በሬ እስከ ገበሬ የሚያክሉ፤ ቢፈልጧቸው ሁለት ሰው የሚወጣቸው ጎረምሶችና ወጣቶች ከካህናቱ በላይ አደግድገው" እንደሚያገለግሉ ያስረዳል። የዳንኤል ጽሑፍ፣ በቀላሉ ምላሽ የማይገኝላቸውን ጥያቄዎቸንም አንስቷል፤ "ለመሆኑ እነዚህ ወጣቶች ማን ለዚህ አገልግሎት መረጣቸው? እንዴት ሊሰበሰቡ ቻሉ? ይህኛውን ዓይነት አገልግሎት ለምን መረጡት? የገንዘብ ምንጫቸው ከየት ነው? እንዴት እንደ አሸን በአንድ ጊዜ በሁሉም የሀገሪቱ ቦታዎች ሊፈሉ ቻሉ?" ይህ ጥናት፣ በዚህ ክፍል ለእነዚህና ሌሎች ጥያቄዎችም እንደሚከተለው ምላሽ ይሰጣል።

ዲያቆን ታደሰ ወርቁ[14] የወጣቶቹ አመጣጥ በሚመለከት፣ "ከጅማው የክርስቲያኖች ጭፍጨፋ ቁጭት እና ከሚሊኒየሙ ክብረ በዓል ጋር ተያይዞ በጣም እየጮኸ ለመጣው አክራሪ እስላምና ምላሽ ነው። ወጣቶቹ በጥምቀት ሰሞን ስለተከሰቱ ‹መጥምቃዉያን› እያሉ የሚጠሯቸዉ አሉ " በማለት ያስረዳሉ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዋና ሙዚየም ኃላፊ የሆኑት ዲያቆን ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል የጥምቀት ተመላሾችን አፈጣጠር በሚመልከት፣ "በሚሊኒየሙ ክብረ በዓል፣ በመንግሥትና በሕዝቡ ውስጥ የተፈጠረውን መነቃቃት ለማስቀጠል በመፈለግ፣ ወጣቶቹ በ2000 ዓ.ም. ጥምቀት በዓል ላይ በአዲስ አበባና በጥቂት የክፍለ ሀገር ከተሞች... በደሴ፣ በጎንደር፣ በባህርዳር፣ በድሬደዋ... ከዚህ በፊት ባልተለመደ ሁኔታ ተከሰቱ..." በማለት አብራርተዋል።

[14] በወቅቱ፣ በማኅበረ ቅዱሳን *የስመ ጽድቅ ጋዜጣ* ከፍተኛ ሪፖርተር ነበሩ (ጥር 21 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

ሁለቱ ባለሙያዎች እንዳሉት፣ በ1990ዎቹ መጨረሻ አካባቢ በጅማ የእስልምና እምነት ተከታይ በሆኑት አክራሪዎች የተፈፀመው፣ የክርስቲያኖች ጭፍጨፋ ከተሰማ ጊዜ ጀምሮ የክርስትና እምነት ተከታዩን ብቻ ሳይሆን፣ ሌላውንም ሕዝብ አስቆጥቷል፡፡ ጭፍጨፋውን የሚያሳየው ምስልም ውስጥ ለውስጥ ሲታይ፣ ከምን ጊዜውም በላይ ሀገሪቱን የሃይማኖት ግጭት በእጅጉ ሊፈትናት እንደሚችል ፍንጭ የሰጠ አጋጣሚ ተደርጎ ተመዝግቧል[15]።በሌላ በኩል፣ "ከምርጫ 97" ጋር ተያይዞ የተቃዋሚ ፖርቲ መሪዎች በእስር ላይ በመሆናቸው ሕዝቡ ውስጥ ውስጡን ያጎመጉም ነበር፤ "በዚህ ሁኔታ ላይ ሁለት ሺህ ዘመን ሲብት የጭቅጭቅ ዘመን ሆኖ ነበር የባተው፡፡ በአገልጋዮች እና በተገልጋዮች መካከል አያሌ ክርክሮች ነበሩ። በተለያዩ እምነቶች መካከልም ደም ያፈሰሱ ግጭቶች ተከስተው ነበር" (ዳንኤል 2003፡1)። ከሁሉም በላይ በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የኑሮ ውድነት ለመጀመሪያ ጊዜ መከሰቱም፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጣራ እየነካ መምጣቱም ይታወሳል። በሕዝቡ ውስጥ ጥርጣሬና ዘረኛ አስተሳሰብ እንዲፈጠር "የኢህአዴግ ብሔር ተኮር የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ" ትልቅ ድርሻ እንዳለው በግልፅ ማጋገሪያ ሆነ (ገዛኸኝ 2004፤ ልደቱ 2003)።

የእነዚህ ሁሉ ሀገራዊ ትኩሳቶችን ለማብረድ በሚል ይመስላል፣ መንግሥት የተቃዋሚ ፖርቲ መሪዎችን ይቅርታ በማድረግ ከፈታ በኋላ፣ በደማቅ ሁኔታ ባከበረው የ፪ሺኛ (ሚሊኒየም) ዓመት በዓል፣ ከምንጊዜውም በላይ ሀገር ወዳድና አፍቃሪ አንድነት መስሎ፣ "ጨርቅ ነው" ያላትን ባንዲራ "የባንዲራ ቀን" ሁሉ ሰይሞ፣ ኢትዮጵያ የ3ሺ ዓመት ባለታሪክ መሆኗን በይፋ ለፈፈ (በሁለት ሺኛ ዓመት በሚሊኒየሙ አዳራሽ በተዘጋጀው ታላቅ ድግስ ላይ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ያቀረቡትን ንግግር ያስታውሷል)።

በዚህ ጊዜ የኤርትራው ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂን ጨምሮ የተለያዩ የመንግሥት ተቃዋሚዎች፣ "ሚሊኒየሙ ለአማራና ለትግራይ ክርስቲያኖች እንጂ ለኦሮሞው፣ ለደቡብ ሕዝቦች እና ለእስልምና እምነት ተከታዮች ምናቸው ነው?" እያሉ በመቀስቀሳቸው እና/ወይም በሌላ ምክንያቶች፣ አብዛኛው የሙስሊም እምነት ተከታዮች "ሚሊኒየሙ" ምናቸውም እንዳልሆነና እነሱን እንደማይመለከታቸው በተለያየ መንገድ ማስተጋባት እንደጀመሩ፣ ውስጥ ለውስጥ መናፈስ ጀመረ፡፡ አንዳንድ የእስልምና እምነት ተከታዮችም አቋማቸውን በይፋ ማራመድ ጀምረው እንደ ነበረ ይታወሳል፡፡ "1987ን እንደመስታወት" ፣ "የኢትዮጵያ ሙስሊም የት ነው?" እና "ለምን ትፈራለህ?" ዓይነት ከረር ያሉ የቅስቀሳ ርእሶችን፣ በዚያው ሰሞን በወጡ የሙስሊም ልሳኖች ላይ ያነበበ ዜጋ፣ የነገሮቹ አካሂያድ የሚሰወሩበት አይመስልም።[16]

የጅማው ቁርሾ ተዳፍኖ ባለበት፣ ሙስሊሙ ኅብረተሰብ "ሚሊኒየሙ እኔን አይመለከተም አለ" መባሉ፥ በተለይ በመስከረም 2000 ዓ.ም. ላይ ተጋግሞ የሕዝቡ የመወያያ አጀንዳ ሆኖ ነበር ማለት ይቻላል። እነ ዲያቆን ታደሰ፣ የወጣቶቹ እንቅስቃሴ በዚያው ዓመት (በ 2000 ዓ.ም.) በጥምቀት ላይ የተከሰተ የጥምቀት ተመላሾች እንቅስቃሴ ነው ቢሉም፣ የዚህ ጥናት አቅራቢ ግን፣

[15] ***ብዕር*** ን (ቅጽ 1፣ ቁጥር 6፣ 2002 ዓ.ም.) ይጠቅሷል፡፡

[16] ***የሙስሊሞች ጉዳይ*** (ቅጽ 2 ፣ቁጥር 16 ጥር 2004 ዓ.ም.) መጽሔትን ይመልከቱ።

በመስከረም 17 የመሰቀል በዓል ዕለት፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ወጣቶቹ ገንዘብ እየለመኑ አካባቢያቸውን አፅድተው፣ ሳር ጎዝጉዘው፣ የአራት ኪሎ ሰፈር ወጣቶች እንዲያውም ድንኳን ሁሉ ተክለው ማክበር መጀመራቸውን ያስታውሳል።

በየሰፈሩ ከደመራ በዓል ጋር ተያይዞ የተጀመረው የወጣቶቹ እንቅስቃሴ በተወሰነ መልኩ ተደራጅቶ፣ በጥር ወር በጥምቀት በዓል ላይ ከወትሮው በተለየ መልኩ ታየ። እነዚህ ወጣቶች፣ ሠንደቅ ዓላማና አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለም ያላቸው ማስዋቢያ ጨርቆችን በገመድ ወጥረው ጎዳናዎችን ማሳመር የጀመሩት በዚሁ ዓመት ነበር። በርግጥ እንደ ኋለኞቹ ዓመታት ብዙ አካባቢዎችን አላዳረሱም፡፡ በዚህ ጊዜ፣ የዚህ ጥናት አቅራቢ ያስገረመዉን አንድ ነገር አስተዋለ[17]፡፡ ወጣቶቹ ከአራት ኪሎዉ ቤተ መንግሥት አጥር ላይ ተንጠላጥለው፣ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለም ያላቸው ቁርጥራጭ የማጌጫ ጨርቆች የያዙ ገመዶች ሲያስሩ፣ ለወትሮዉ በግንቡ ተጠግቶ የሚሄድን ሰው የሚያባርሩ[18]የቤተ መንግሥቱ ጠባቂዎች እያዩዋቸው ዝም ማለታቸውን ታዝቦ፣ አንዳች የሆነ ጥያቄ አጭሮበታል።

እዚህ ላይ ከእስከ ዛሬ የሕይወት ልምዳችን እንደምንረዳው የቤተ መንግሥት ጠባቂ ወታደሮቹ ከበላይ ባለሥልጣን ትዕዛዝ ሳይተላለፍላቸው፣ ወጣቶቹ የቤተ መንግሥትን "ድንበር ሲዳፈሩ" ዝም እንደማይሏቸው መገመት አይከብድም። ይህን አስመልክቶ ዲያቆን ታደሰ፣

> በወቅቱ አክራሪ እስልምና እየፎኸ መምጣቱ መንግሥትንም ያበሳጨው ይመስላል። እናም ቁጡ ሐዋሪያቱን ወይም የጥምቀት ተመላሾቹን ‹social balance› ማኅበራዊ መመጣን ለመፍጠር የተጠቀመባቸው ይመስለኛል። በ2001 ዓ.ም. ላይ ወጣቶቹ ከአምናው በተሻለ ተጠናክረው ተደራጅተው ሲመጡ ግን፣ ለሱም ስጋት ሁነውበት ነበር፡፡ የጥምቀት ተመላሾቹ ችግራቸውን የሚፈቱት በጉልበት ነው፡፡ ሥራቸውን በድፍረትና በኃይል ነው የሚፈጽሙት… አንዳንድ ሰዎች እንደውም ‹ቁጡ ሐዋሪያ› ይሏቸዋል። ቢፈራቸው አይፈረድበትም፤ በኋላ ላይ እንደውም ከእነዚህ ወጣቶች ጀርባ ማኅበረ ቅዱሳን አለበት በሚል እነ አባይ ፀሐዬ[19] በዝግ ሰብስበው አነጋግረውናል፤ ለማስፈራራትም ሞክረዋል …

የሚል አስተያየት ሰጥተዋል።ዲያቆን ታደሰ እንዳሉት፣ የ2001 ዓ.ም. ጥምቀት፣ ወጣቶቹ የበለጠ ተደራጅተው በዝተውና ትልቅ የገንዘብ አቅም ፈጥረው ነበረ የተከሰቱት። በ 2000 ዓ.ም. ብዙም ያልታዩ በአብዛኛው አረንጋዴ፣ ቢጫና ቀይ ከናቴራ የለበሱ "ቁጡ ሐዋሪያዎች" በርግጥም፣ በክብረ በዓሉ ላይ ጎልተው ታይተዋል። መንግሥትንና በአብዛኛው የእስልምና እምነት ተከታዮችን ያስቆጣውና ያስበረገገው ግን፣ ከናቴራ መልበሳቸው ብቻ አልነበረም፤ በከናቴራቸውና በባነራቸው

---

[17] በወቅቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ የድኅረ ምረቃ መምህሩ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ የጥምቀት በዓል አከባበርን እንዲዘግብ የሰጡት የቤት ሥራ በፈጠረበት መነቃቃት፣ የክብረ በዓሉን እንቅስቃሴ በትኩረት እየተከታተለ ማስታወሻ ይይዝ ነበር፡፡

[18] የዚህ ጥናት አቅራቢም፣ አንድ አይሉ ሁለት ጊዜ አጋጥሞት ያውቃል፡፡

[19] በወቅቱ የፌድራላ ጉዳዮች ሚኒስቴር "የበላይ ጠባቂ" እና የቀድሞ የህወሓት ታጋይ የነበሩ፣ "መንግሥት ከጥቀምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በትግራይ ክልል ላይ ባደረገው ሕግ የማስከበር እርምጃ የተገደሉ…" ሰው ናቸው፡፡

ላይ ያተሟቸው ጥቅሶች ጭምር እንደነበሩና በፓርላማዉ ላይም "የመወያያ" አጀንዳ እስከ መሆን እንደደረሱ ይታወሳል፡፡ ከሁሉም በላይ "ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት!"፣ "አንድ ሀገር፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ጥምቀት!"[20] የሚሉት ጥቅሶችና የወጣቶቹ ጉልበተኝነት[21]፣ መንግሥት፣ ያውም በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተነገረ ወቅታዊ መግለጫ እስከ ማውጣት መድረሱን ያስታውሷል።

በዚያው ዓመት የጥምቀት ተመላሾች ስሜታዊነት በተቀላቀለበት ሁኔታ፣ በአብዛኛው "ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት" የሚለውን ጥቅስ[22] ይዘው ብቅ ያሉት፣ ኅዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም. በፓርላማ ይፋ የሆነው የሕዝብ ቆጠራ በፈጠረው ውዥምብር ጭምር ይመስላል። የሕዝብ ቆጠራው ውጤት፣ ሃይማኖቶችን፣ ክልሎችና ብሔሮችን ማዕከል አድርጎ አጨቃጭቋል። ከሁሉም በላይ ግን የእስልምና እምነት ተከታዮች፣ ኦርቶዶክስ 43.5% ተብሎ፣ ሙስሊሙ 34% ነው መባሉን በይፋ ተቃወሙ። እንደውም፣ "ከሀገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ ከግማሽ በላይ ሙስሊም ነው" በማለት የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑትን፣ የወቅቱን የስታትስቲክስ ኤጀንሲ ዳይሬክተር ወ/ሮ ሳኒያ ዘካሪያን እስከ ማብጠልጠል ደረሱ፡፡ ወ/ሮ ሳኒያም "በአንድ ላይ ወጥተን፣ ሂጃብ ለብሰን ስንታይ የበዛን ሊመስለን ይችላል፡፡ ቆጠራው ግን ሳይንሳዊና ትክክል ነው..." በማለት የመለሱበት የፓርላማ መድረክ፣ በሀገሪቱ ውስጥ በተለይ በኦርቶዶክስና በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ትልቅ ውዥንብር መፍጠሩ ይታወሳል (ዮሐንስ 2001፡5)፡፡ ስለዚህ፣ የጥምቀት ተመላሾች ጥቅስ፣ ለዚህ ትኩሳት ማስታገሻ "መልስ ነው" የሚለው አመክንዮአዊነት (logicality) አለው ማለት ይቻላል።

ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ በየአቅጣጫው ነገር መለኮሱን መግንሥት በይፋ ባይናገረውም፣ ያስፈራው ይመስል ነበረ፡፡ በተለይ፣ የጥምቀት ተመላሾቹ እንቅስቃሴ፣ ‹በተደራጀ መንገድ ቀስ እያለ የሚሄድ የፖለቲካ ጥያቄ ነው› ብሎ እንዲያስብ አደረገው፡፡ ለዚህ ነው፣ "ማኅበረ ቅዱሳን፣ በምርጫ 97 ብዙ ድምጽ እንዳጣ ማድረጉ ሳያንስ፣ አሁንም እነዚህን ወጣቶች እያደራጀብኝ ነው..." በሚል ከማኅበሩ ጋራ ውስጥ ለውስጥ ይቆራቆስ የነበረዉ (ገዛኸኝ 2001)፡፡ እዚህ ላይ፣ በጥር ወር፣ 2001 ዓ.ም. ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችን የሚከታተል የሃይማኖት ጉዳይ ዘርፍ በትምህርተ ሚኒስቴር ሥር ከማቋቋም አልፎ፣ በየካቲት ወር፣ 2001 ዓ.ም. "የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ" እስከ ማርቀቅ መድረሱ፣ ከየጥምቀት ተመላሾች እንቅስቃሴ ጋር ይገናኝ ይሆን? ብሎ መጠየቅም፣ ማጠየቅም ይገባል።

እዚህ ላይ፣ መንግሥታት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ አዳዲስ የፎክሎር ዘውጎች እና ማኅበረ ባህላዊ ዐውዶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ይሆናሉ ማለት ይቻላል። ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው፣ እነ

---

[20] አባሪ "ሀ" ን ይመልከቱ፡፡

[21] ለምሳሌ በጎንደር ከተማ የሚካኤል ታቦት ሲገባ፣ የጥምቀት ተመላሾች ከሙስሊም ወጣቶቹ ጋራ ግጭት ፈጥረው በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት እንደደረሰ፣ ጥር 13፣ 2001 ዓ.ም. ምሽት ላይ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በሁለት ሰዓት ዜና መቅረቡ ይታወሳል፡፡

[22] በዚህ ዐውድ "መፈክር" ሊባል ይችላል፡፡

ሳሊበላ ለሃይማኖታቸው ቀናኢ ስለሆኑ፣ ኢህአዴግ ሥልጣኑን የሚወድና የሚያቆይበት አፋኝ ሥርዓት የዘረጋ በመሆኑ (መስፍን 2002፤ ልደቱ 2002 ያመሳከሯል) አዳዲስ የባህል ገጽታዎች ለመፈጠር ምክንያት ሆኑ፡፡ የጥምቀት ተመላሾች፣ ወቅታዊውን የፖለቲካ ትኩሳት በፊት ለፊት የሚናገሩበት መድረክና የሚያደምጥ ሥርዓት ቢኖር ኖሮ፣ በሕገ መንግሥቱ (አንቀጽ ፲ን ይመለከቷል) ላይ፣ መንግሥት ጣልቃ የማይገባበት ጉዳይ እንደሆነ የተገለፀውን፣ "ሃይማኖትን" እንደከለላ ለመጠቀም እና ከመንግሥት የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ትይዩ፣ መንግሥት ሊነካው የሚፈራውን ሃይማኖት ተኮር ሌላ አደረጃጀት ለመፍጠር ባልቻሉ ነበር።[23]

የጥምቀት ተመላሾች በየዓመቱ አደረጃጀታቸውን እያጠናከሩ መጥተዋል፡፡ በ 2002 ዓ.ም. የመንግሥት መግለጫን ተከትሎ ቤተክህነት የጥምቀት ተመላሾች፣ "ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት" ዓይነት ተንኳሽ ጥቅሶችን እንዳይጠቀሙ በየአጥቢያው መግለጫና ትምህርተ ሃይማኖት እንደሰጡ ዲያቆን ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል ይናገራሉ። በ 2002 ዓ.ም. የጥምቀት ተመላሾች እንቅስቃሴ ሀገር አቀፍ መልክ ለመያዝ እንደበቃ፣ የወጣቶቹ ተሳትፎ ከሚጠበቀው በላይ እየጨመረ እንደመጣ ለማንም ግልጽ ነበር፤ ለምሳሌ፣ ከ 500 መቶ ሜትር ያላነሱ ቀያይ ምንጣፎችን ገዝተው፣ የየደብሩ ታቦታት በምንጣፉ ላይ እንዲያልፉ በማድረግ ከአስርት ዓመታት በኋላ በቁሳዊ ፎክሎርነት ሊጠና የሚችል፣ ከዚህ ቀደም በሥራተ እምነቱ ክዋኔ ላይ ታይቶ የማይታወቅ "አዲስ ቁስ" ያስተዋወቁት በ 2002 ዓ.ም. መሆኑን አጥኚው ከፊል ተሳትፏዊ ምልከታ ባደረገበት በጃንሜዳ የጥምቀት ሥራተ እምነት ላይ አስተውሏል፤ በማስታወሻው መዝግቧልም፡፡

በ 2002 ዓ.ም.ጥምቀት ላይ የጥምቀት ተመላሾቹ፣ "ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት" የሚለውን ጥቅስ አብዝተው ባይጠቀሙም፣ "ኢትዮጵያ በድንግል ማርያም የተባረከች ሀገር ናት" የመሳሰሉ ሌሎች መልካቸውን የቀየሩ ተመሳሳይ ጥቅሶችን[24] ለብሰው ታይተዋል፡፡ በ 2003 ዓ.ም. በተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ የጥምቀት ተመላሾች በ 2002 ሲያከናውኑ የነበሩትን ተግባራት አጠናክረው መቀጠላቸው ታይቷል። በርግጥ ዲያቆን ዳንኤል ከብረት እንደሚናገሩት ከሆነ፣ "ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት" የሚል ጥቅስ ያደረገ አንድም ሰው ማየታቸውን አያስታውሱም። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ግን፣ በአክሱም ከተማ ሁለት የአክሱም ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የተባለውን ጥቅስ የያዘ ከናቴራ ለብሰው እንዳጋጠሙት እና "የዓምና ቲሸርት ነው..." እንዳሉት ያስታውሳል። ዲያቆን ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል፣ "አንድም ሰው፣ የተባለው ጥቅስ የታተመበትን ቲሸርት ለብሶ አይወጣም ማለት እንደሚከብድ..." እና እርሳቸውም በሰፈራቸው አንድ ወጣት እንዳጋጠማቸው ለአጥኚው ነግረውታል።

---

[23] ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንግሥት በመስከረም ወር 2004 ዓ.ም. የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ተማሪዎችን፣ "ልማት ዲሞክራሲና የሃይማኖት አክራሪነት" በሚል ሲያወያይ፣ በእስልምና ሃይማኖት ሽፋን ሙስሊም ወጣቶችን መልምለው እያደራጁ እስላማዊ መንግሥት ለመመሥረት የሚንቀሳቀሱ አክራሪዎች መኖራቸውን፣ ማኅበረ ቅዱሳንም፣ "ከቤተ ክርስቲያኗ የበላይ ጠባቂ ከቅዱስ ሲኖዶስ ጭምር ያፈነገጠ፣ የነፍጠኛ ሥርዓት ናፋቂ ሕገ ወጥ ቡድን ነው..." ብሎ የፈረጀው መሆኑን በአጽንኦት መግለጹና የማምከኛ ሰነድ ጭምር ማዘጋጀቱ ይታወሳል።

[24] አባሪ "ለ" ን ይመልከቱ።

ዲያቆን ታደሰ ወርቁ እንደሚሉት፣ አብዛኞቹ ወጣቶቹ ለሃይማኖታቸው ያላቸውን ቀናኢነት እስከ መስዋዕትነት ጭምር እንደሆነ የሚገልፁ፣ በብዙ መልኩ "ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት" ከሚለው የሚበልጡ አዳዲስ ተንኳሽ ጥቅሶች መጠቀማቸውን እንደተመለከቱ ተናግረዋል[25]። በዚያው ዓመት፣ ከፖትርያሪኩ ጀምሮ በየደረጃው ያሉ የቤተክህነት ሰዎች በየቤተ ክርስቲያኑ የየአጥብያው የጥምቀት ተመላሾችን ጠርተው በመምከራቸውና ሊያስጠይቃቸውም እንደሚችል በማስጠንቀቃቸው፣ በ 2004 ዓ.ም. ሁሉም ማለት በሚያስችል ደረጃ ጥቅሶችን ከ*መጽሐፍ ቅዱስ*ና ከሌሎች የቀኖና መጻህፍት መውሰዳቸውን ገልጸዋል (ዝርዝሩን፣ በተከታዩ ክፍል ይመልከቱ)።

**የጥምቀት ተመላሾች እንዴት ነው የተደራጁት?** የሚለው ጥያቄም የብዙዎች ጥያቄ ነውና ምላሽ ይፈልጋል። ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፣ "በየሰፈራቸው በማኅበር ነው የተደራጁት" ይላሉ። ዲያቆን ታደሰና ዲያቆን ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል ደግሞ አደረጃጀታቸው ሦስት ዓይነት መልክ እንዳለው ያስረዳሉ፤ አንዳንዶቹ በየአካባያቸው ባሉ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተደራጅተው ለመታቀፍ ይጥራሉ። ሌሎቹ ደግሞ፣ የሰንበት ትምህርት ቤትን አይፈልጉም። በፃድቃን በሰማዕታት ስም ለምሳሌ፣ በሚካኤል፣ በተክለሃይማኖት ስም ወዘተ. ማኅበር መሥርተው በየወሩ ጸበል የሚጠራሩ ናቸው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ የምናያቸው ደግሞ፣ የየሰፈሩ አብሮ አደግ ወጣቶች፣ በጥምቀት ሰሞን ተሰባስበው የሚመሠርቷቸው መዋቅሮች እንደሆኑ የምርምር ተሳታፊዎቹ ገልጸዋል፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢም፣ የተለያዩ ሰዎችንና የጥምቀት ተመላሾቹን በመጠየቅ ከላይ በተገለፁት በሦስቱ መንገዶች መዋቅር ፈጥረው ገንዘብ እንደሚያሰባስቡ አረጋግጧል[26]።

**የጥምቀት ተመላሾች  የተለያዩ ተግባራትን የሚያስፈፅሙበት ገንዘብ የት ይገኛሉ?** የገንዘብ ምንጫቸው ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችም ይነሳሉ። አጥኚው፣ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመጠየቅና በአካባቢው ካሉት ወጣቶች ጋር በመሳተፍ የገንዘብ ምንጫቸውን ለማወቅ ሞክሯል። በሰንበት ትምህርት ቤቶችና በጻድቃን ሰማዕታት ስም በተቋቋሙ ማኅበራት የተደራጁ የጥምቀት ተመላሾች ይብዛም ይነስም፣ ወርሃዊ መዋጮ ያደርገሉ። በየአካባቢው  የጥምቀት በዓል ሲቃረብ ተጠራርተው የሚደራጁት ወጣቶች ደግሞ፣ በተለያየ መንገድ ገንዘብ ይለምናሉ። በሦስቱም መንገድ የተደራጁ የጥምቀት ተመላሾች አንድ የሚያደርጋቸው ግን፣ በየአካባቢያቸው ያሉ ታዋቂ ሰዎችንና ባለሐብቶችን በየቤታቸው እየዞሩ እንዲያዋጡ ማድረጋቸው ነው፤ ተጨባጭ ሥራ ሠርተው እንደሚያሳዩዋቸውም ጭምር በማግባባት፣ ገንዘብ ለማግኘት ይጥራሉ። ለክብረ በዓሉ ማድመቂያ የሚሆኑ የተለያዩ ቁሳ ቁሶችን ሱቅ ካላቸው ከሱቃቸው አንስተው እንዲሰጧቸው፣ የሌላቸው ከሆኑ ደግሞ ገዝተው እንዲያመጡላቸው ሁሉ ሲያደርጉ አጥኚዉ ተመልክቷል።

ወጣቶቹ፣ ከማስገደድ ባልተናነሰ በመንገድ ላይ አልፎ ሂያጆችን እያስቆሙ ሲለምኑ ይታያል። የዚህ ጥናት አቅራቢ መኪኖችን በማስቆምና በማንገራገር ጭምር ገንዘብ የሚቀበሉ፣ "የጥምቀት

---

[25] አባሪ "ሐ" ን ይመልከቱ፡፡

[26] አጥኚው ያረጋገጠው፣ በአዲስ አበባ የጃን ሜዳና የዙሪያው ሰፈር የጥምቀት ተመላሾችን አደረጃጀት በሚመለከት ነው፡፡

ተመላሾች" አጋጥመውታል። በተለይ የበዓሉ ሰሞን ተጠራርተው የሚደራጁት ወጣቶች፣ በአብዛኛው ሥራ አጥ ስለሆኑ፣ አጋጣሚውን ገንዘብ የማግኛ ምንጭ ለማድረግ የሚፈለጉ እንደሆኑ ታይቷል- ይጠበቃልም። አጥኚው፣ ቅዳሜ ጥር 12 ቀን 2004 ዓ.ም. የሚካኤልን ታቦት ሲሸኝ፣ በአካባቢው ከነበሩት የጥምቀት ተመላሾች መካከል ስድስት ኪሎ አንበሳ ግቢ አካባቢ ሲደርሱ እየዘመሩና ከናቴራቸውን እንዳደረጉ ጫት ሲገዙ አጋጥሞታል። አንበሳ ግቢው ፊት ለፊት ወደ ምንሊክ ሆስፒታል በሚወስደው መንገድ ላይ የነበሩ "የጥምቀት ተመላሾች" ደግሞ፣ ግማሾቹ እየዘመሩ፣ ሌሎቹ ጫትና ኮካ ይዘው ወደ ሠሩት ድንኳን ሲገቡ ተመልክቷል። እዚሁ ቦታ ላይ ካሉ ጫት ቤቶች፣ አንድ ዓይነት ከናቲራ ያደረጉ የአንድ ሰፈር ቡድን አባላት ("የጥምቀት ተመላሾች")፤ ኮካ፣ የታሸገ ቆሎ፣ አቾሎኒና ጫት በታክሲ አስጭነው ሲወስዱ ነበር[27]።

ለዚህ ይመስላል፣ የጥምቀት ተመላሾቹን ወደ ቤተክህነት ለማምጣት ሲፈለግ፣ ችግሮች የሚፈጠሩት፡፡ ብዙዎቹ የሃይማኖት ተቋሚትን ሥነ ምግባርና አስተምህሮ ለማክበር የማይችሉ፣ ለወደፊቱም መላ ካልተበጀላቸው ለቤተ ክርስቲያኗም የጥፋት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ፣ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኗን አለመኖር የሚፈልጉ ሌሎች አካላት በገንዘብ ደልለው ወደ ጥፋት እንዳያሰማሯቸውና እንዳይጠቀሙባቸው የሚያሰጉ እንደሆኑ፣ የምርምር ተሳታፊዎቹ አስረድተዋል።

በሌላ በኩል፣ ፓትርያሪኩን ጨምሮ በቤተክህነት ውስጥ በብሔርና በተለያየ ጥቅማጥቅም ቡድን የፈጠሩ አካላት እርስ በረስ ሲወነጃጀሉ፣ የጥምቀት ተመላሾችን በየራሳቸው ጎራ ለማሰለፍ ይሽቀዳደሙ እንደነበረ ጥናቱ ተመልክቷል (ዘኤልያስ 2004)። አንዳንድ ዘማሪያንና የቤተክህነት ሰዎች ከየአካባያቸው የተወሰኑትን የጥምቀት ተመላሾች እየመረጡ፣ እንደ ጠባቂ ("ቦዲጋርድ") ጭምር ለመጠቀም መሞከራቸው አልቀረም። ለምሳሌ፣ ዘማሪ ትዝታው ሳሙኤል፣ ሌሎች ዘማሪያን በላኳቸው የጥምቀት ተመላሾች እንደተደበደበ፣ ዲያቆን ታደሰ ማስረዳቱን ያስታውሷል።

ባጠቃላይ አጥኚው፣ በዋናነት በ 2004 ዓ.ም. የጥምቀት በዓልን ለማክበር በወጡት ወጣቶች ከናቴራ እና "ባነሮች" ላይ የተፃፉ፣ በአብዛኛው መጽሐፍ ቁዱሳዊ የሆኑ ጥቅሶችን ከሀገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታዎች (ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች) ጋር እያናበቡ መተንተንና መፈከር ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ አስቦ የነበረ ቢሆንም፣ የጥቅሶቹን ምንነትና ተግባር በወጉ ለመረዳት ሲባል ግን፣ የጥቅሶቹን አዘጋጆች፣ የጥምቀት ተመላሾቹን የማንነት ዳራ ከዚህ በላይ በቀረበው መሠረት በዝርዝር ለመፈተሽ ጥረት አድርጓል፡፡ በዚህም፣ ስለ ወጣቶቹ ሀገረሰባዊ ቡድኖችም ሆነ ሥለ ጥምቀት ሥራተ ክዋኔዎች አዳዲስ ፎክሎራዊ ዕውቀቶች የማጠናቀርና ሃይማኖታዊ ርእስ ጉዳዮችን ማንጸር የሚያስችሉ የምርምር ተመክሮዎችን የመቅሰም መልካም አጋጣሚዎች እንደተፈጠሩለት በመግለጽ፣ ወደሚቀጥለው ክፍል ይሻገራል፡፡

[27] ሐሊና (2010፡80)፣ በጥምቀት በዓል "የጃንሜዳ ሀርሞኒካ ከዋኞች ሙሉ ለሙሉ ማለት በሚቻልበት ሁኔታ በብዙ ጠጥተዋል፡፡ አብዛኞቹም ጭፈራው ላይ ተሳታፊ የነበሩ ወጣቶች ሲጋራ ያጨሳሉ" ማለታቸውን ያመሳክሯል፡፡

**4. የጥምቀት ተመላሾች ጥቅሶች ፍካሬ**

በቀዳሚው ክፍል፣ የጥምቀት ተመላሾች ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ በአልባሳትና "በባነሮች" ላይ ያሰፈሯቸውን ጥቅሶች ለምን ዓላማ እንደተጠቀሙባቸውና ምንስ እንዳስከተሉባቸው፣ እነርሱም ከየት ተነስተው የት እንደደረሱ ብሎም፣ በ2004 ዓ.ም. ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ *የመጽሐፍ ቅዱስ* ጥቅሶችን እንዲጠቅሱ እስከ መገደድ መድረሳቸው ተቃኝቷል። በዚህ ክፍል ደግሞ፣ ከጥር 7 እስከ ጥር 12 ቀን 2004 ዓ.ም. በጃንሜዳና በዙሪያው ባሉ አካባቢዎች፣ የጥምቀት ክብረ በዓልን ለማክበር ከወጡ የጥምቀት ተመላሾች ከናቲራዎች/ቲሸርቶች እንዲሁም ለየድንኳኖቻቸው እና መድረኮቻቸው ካሠሯቸው (ከሰቀሏቸው) "ባነሮች" ላይ የተሰበሰቡ 40 ጥቅሶች ተተንትነዋል።

እነ ሹሜከር፣ "The most important step towards analysis, however, is to *study* the material that you yourself have collected" (Schoemaker 1990:29) በማለት በመከሩት መሠረት፣ አጥኚው፣ ከየ ሁኔታዊ ዐውዶቻቸው ጋራ የሰበሰባቸውን ጥቅሶች እያገላበጠ ካጠናቸው በኋላ፣ የጥምቀት ተመላሾቹ ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ ከተጠቀሙባቸው ሌሎች ጥቅሶች ጋራ እያናበበ፣ የፈጠሩትን ፈሮች (patterns) በመለየትና በመከተል በ2004 ዓ.ም. ተግባራዊ ከሆኑ *የመጽሐፍ ቅዱስ* ጥቅሶች ጫፍ ደርሷል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶቹን ለመተንተንና ለመፈከር ደግሞ፤ የምርምር ተሳታፊዎቹ ደጋግመው ያነሷቸውና አጥኚው በየዐውዶቹ በማስታወሻው ያሰፈራቸው መረጃዎች[28]፣ ዋና ማተኮሪያ ሆነዋል፡፡ አጥኚው እራሱ የክብረ በዓሉ ተሳታፊ በመሆን፣ ከተለያዩ ወጣቶች ስብስብ ጋራ የመወያየትና ሥራት እምነቶችን የመከወን ዕድል ማግኘቱ፤ የጥምቀት ተመላሾቹ፣ ጥቅሶቹን ከየትና እንዴት እንዳገኟቸው፣ ምን ማለት እንደሆኑ፣ ለምን እንደሚጠቀሙባቸው ወዘተ. መረዳት አስችሎታል፡፡

ጥቅሶቹ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ፣ ክርስቲያናዊ መሠረት አላቸው፤ እንዲያውም፣ "መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው" ማለት ይቻላል፡፡ በርግጥ፣ ሁሉም የጥቅሶቹ ቃላት ከ*መጽሐፍ ቅዱስ* ላይ በቀጥታ የተቀዱ አይደሉም፡፡ በተለይ ከናቲራ/ቲሸርት ላይ የታተሙት ጥቅሶች አጠር አጠር የማለት ባህርይም ታይቶባቸዋል፡፡ ከአልባሳቱ መጠነ ጥበት የተነሳ ይመስላል፣ በምዕራፍና ቁጥር የተቀነበበዉን ዐረፍተ ነገራዊ ምጣኔና መልእክት ሳይጠብቁ፣ ጥቅሶቹን ከሚፈልጉት ቦታ ላይ ቆርጠዉ ሲጠቅሱ ይታያል፡፡ ለምሳሌ፣ ከአንድ የጥምቀት ተመላሾች ቲሸርት ላይ የታተመው ጥቅስ፣ "የፃድቅ ሰው ጸሎት በሥራው እጅግ ሀይል ታደርጋለች ያዕቆብ ፭÷፲፮" ይላል (አባሪ "ሠ"ን ይመልከቱ)፡፡ ጥቅሱ የተወሰደው፣ ከያዕቆብ መልእክት፣ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 16 ላይ ሲሆን፣ በምዕራፉና በቁጥሩ ተወክሎ የሰፈረው ሙሉ ጥቅስ፣ "እርስ፡ በእርሳችሁ፡ በኃጢአታችሁ፡ ተናዘዙ፥ ትፈወሱም ዘንድ፡ እያንዳንዱ፡ ስለ፡ ሌላው፡ ይጸልይ፤ የጻድቅ፡ ሰው፡ ጸሎት፡ በሥራዋ፡

[28] ግሬይ (Gray 2004:244) ስለ ተግባራዊ የጥናት ዘዴዎች በጥልቀት ባተቱበት መጽሐፋቸው ላይ Bailey (1996: 80) ጠቅሰው፣ "field notes are 'the backbone of collecting and analyzing field data'" በማለት የመስክ ሥራ ማስታዎሻዎች፣ የመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለመተንተን የጀርባ አጥንት ናቸው ማለታቸውን ያስተውሷል፡፡

እጅግ፡ ኃይል፡ ታደርጋለች፡፡"[29]የሚል ነው፡፡ ስለዚህ፣ በቲሸርቱ ላይ ታትሞ የምናየው ጥቅስ፣ ተቆርጦና የሰዋስው ስሕተት[30] አክሎ የቀረበ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችን፣ ከሌሎች ጥቅሶች ወይም እራሳቸው ካቀናበሯቸው አባባሎች ጋራ አስማምተው፣ ላይና ታች አከታትለው ወይም ጎንና ጎን ሰድረው በአልባሳታቸው እና ብዙ ጊዜ በባነሮቻቸው ላይ አትመው፣ ክብረ በዓላቸውን ሲያደምቁባቸውም ታይተዋል፡፡ ለምሳሌ፣ "አንተ መብራቴን ታበራለህና መዝ. ፲፯÷ ፪፰" የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ እና "ኢትዮጵያ የግዮን መፍለቂያ ቅድስት ሀገር ናት!"[31](አጽንኦቱ፣ የዚህ አጥኚ ነው) የሚለውን ከሌላ ቦታ የተገኘ የሚመስል አባባል፣ ላይና ታች አድርገው በቅደም ተከተል በመሰደር [የፈጣሪያቸውን ቃል ቀዳሚ፣ የፍጡራኑን ቃል ተከታይ ማድረጋቸውን ይፈክሯል] በአንድ ባነር ላይ አሳትመው የያዙ የጥምቀት ተመላሾችም አጋጥመዋል (በአባሪ "መ" ሥር 2ኛውን ጥቅስ ይመለከቷል)፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀመው፣ ዐውድ አንጻራዊነትን ባህርይው ያደረገ የመስፋፋትና የመሰብሰብ ተፈጥሮ ስላለው፣ የጥምቀት ተመላሾቹ በክብረ በዓሉ ላይ ጥቅሶቹን የተጠቀሙበት የወዲያው ሁኔታ፣ በየትኛውም የምልከታ መንገድ ቢሆን "የዐውድ ዐውድ"[32] የሚሆንበት አጋጣሚ ስለማያጣ፣ ከ6ቱ የቦማን የዐውድ ዓይነቶች መካከል ከሁኔታዊ ዐውድ ጋራ እንደሚገጥምም ጥናቱ ተመልክቷል፡፡ ከ*መጽሐፍ ቅዱስ* ላይ የተወሰዱት ጥቅሶች ሲተነተኑ ደግሞ፣ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ከነበሩበት ዐውድ ጋራም ማናበብ ስለሚያስፈልግ፣ የቦማንን ትርጉማዊ ዐውድ ማውጠንጠንና መጠቀም ግድ ብሏል።

የጥምቀት በዓል በራሱ በብዙ ታሪካዊ ሂደቶች ውስጥ አልፎ የራሱ ሥራተ እምነቶችና ትውፊታዊ የከዋኔ ደንቦች እየተከለ ወይም እያቆመ የመጣ ተቋም ነው፡፡ ይህ የሥራተ እምነት ተቋም ደግሞ፣ ሃይማኖታዊ ተቋም የሆነችዉ የኢኦተቤ. አካል ነው፡፡ ስለዚህ አጥኚው፣ የወጣቶቹን ሥራተ ክዋኔ፣ ከጥምቀት ክብረ በዓል ተቋማዊ መልኮች አንጻር እንዲሁም፣ ከቤተ ክርስቲያኗ ማኅበረ

[29] ጥቅሱ፣ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ *መጽሐፍ ቅዱስ* (1980 ዓ.ም.) የተቀዳ ነው፡፡

[30] "የፃድቅ ሰው ጸሎት በሥራው እጅግ ሀይል ታደርጋለች" በሚለው የጥምቀት ተመላሾቹ "ጎዶሎ" ጥቅስ ውስጥ፣ "በሥራው" የሚለው መስተዋድዳዊ ሐረግ፣ "በሥራዋ" ተብሎ በትክክል ባለመቀዳቱ፣ ከፊደል ግድፈት በላይ የሆነ የሰዋስው ስሕተትም አስከትሏል፡፡ በዋናው ጥቅስ ላይ ያለው፣ "በሥራዋ" የሚለው የዐረፍተ ነገሩ ተሳቢ፣ በአነስታይ ጾታ የተነገረ፣ "ታደርጋለች" ከሚለው ግስ ጋራ የሚሠምር ሐረግ መሆኑን ያስታውሷል፡፡

[31] ሁለቱም ጥቅሶች እርስ በእርስ የሚናበቡና መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም. ይፋ የሆነውን የታላቁን ሕዳሴ ግድብ ግንባታ የሚያጎላምሱ ይመስላሉ፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ፣ ሀገረኛ የፎክሎር ምርምሮችን ሲያፈላልግ በድንገት ያገኘው፣ "MYTH AND REALITY: MINDS OF ETHIOPIAN POETS ON THE BLUE NILE» የሚለው የ Bayleyegn (2002) ጥናት፣ ትኩረቱን በዓባይ ወንዝ ላይ ያደረገ ሲሆን፣ ጥናቱ፣ ሚት፣ የሰው ልጅ የረጅም ጊዜ አስተሳሰብ አንዳች የሆነ ፈር ይዞ የሚገኝበት "ሐቅ" መሆኑን አጣቅሶ፣ ("what are the human patterns of thought that bring order to world?" የሚል መሠረታዊ ጥያቄን ለመመለስ የሚታትረውንና በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሆነውን የ Levi-Strauss መዋቅራዊ ፈለግን ማንጸሪያው አድርጎም ይመስላል) የተለያዩ ትእምርቶችን በማስተንተን፣ በግሪክና በግብጽ ሚቶች እንዲሁም በኢትዮጵያውያን ገጣሚዎች አስተሳሰብ ውሥጥ ያለውን "ዓባይ-ተኮር" የኢትዮጵያውያን ቁጭትና ርዕይ አርቅቆ ያመላከተ፣ ቅልብጭ ያለ ሥራ መሆኑን ይጠቁሟል፡፡

[32] ለፎክሎር ምርምር የንድፈ ሐሳብ መሠረት ከሆኑ አዳዲስ ማንጸሪያዎች መካከል፣ "Context in Context" ("የዐውድ ዐውድ" ወይም "በዐውድ ውስጥ ዐውድ") የሚለው የቤን-አምጽ (Ben-Amos 1993) ጥናትን ያስታውሷል፡፡

ባህላዊ ዳራዎች ወይም ከሃይማኖታዊ የአስተሳሰብና የአሠራር ልምዶችና ልማዶች አንጻር ሲፈትሽ፣ የቦማንን ተቋማዊ ዐውድ ማጤኑ ብዙ እንደጠቀመው ያነጽሯል፡፡

በሌላ በኩል ጥናቱ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶቹን ከገናን ይዘቶቻቸው አንጻር ለመፈከር፣ በዐውዳዊ ፈለጉ ማንጸሪያነት የጥምቀት ተመላሾቹን አመጣጥ ዳራ ከሚያስቃኘው ሀገራዊ ዐውድ ውስጥ በብልሃት ተጠንፍፈው ፈር የያዙ ርእሰ ጉዳዮችን መሠረት አድርጓል፡፡ ከዚህ ጋራ ተያይዞም፣ ጥቅሶቹን በተለያዩ ዘውጎች መመደብ፣ ቀዳሚ ተግባር ሆኗል። የዘውጎቹ ምደባ የተሞከረውም፣ በእነ ማሊኒውስኪ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ[33] (functional theory) ማንጸሪያነት፣ ወጣቶቹ ጥቅሶቹን ለምን ለምን ዓላማዎች ማስፈጸሚያነት እንዳዋሏቸው በመለየት ነው፡፡

የጥምቀት ተመላሾቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶቹን፣ ለተለያዩ ፍላጎቶቻቸው ማሳኪያነት ሲጠቀሙባቸው ታይቷል፡፡ በጥቅሶቹ ማንጸባረቅ የፈለጓቸው ጉዳዮች (ይዘቶች)፣ እንደየ ሀገረሰባዊ ቡድኖቹ የተለያዩና የተዘበራረቁ ናቸው፤ በርግጥ፣ ቀደም ሲል በ3 ጥቅሶች ማሳያነት ለማመላከት እንደተሞከረው፣ የቡድኖቹ የጥቅሶች አጠቃቀም ላይ፣ ለምሳሌ ጥቅስ አጻጻፋቸው (ቅርጾቻቸው) ላይ የሚታዩባቸው ልዩነቶች ያህል ግን፣ ብዙ ልዩነቶች (ብዙ ግድፈቶች፣ ብዙ መዘበራረቆች) አልታዩባቸውም ማለት ይቻላል፡፡

ባጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶቹ ላይ ከታዩት ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች መካከል፣ የጥምቀት ተመላሾች ቡድኖቹ አብዝተው የተገለገሉባቸው፣ አምስት ያጠቃቀም መንገዶች በጥናቱ ተለይተዋል። የጥቅስ አጠቃቀም መንገዶቹም፡-

1ኛ. የመጡበትን አካባቢ በአድባራቱ ስም ተምሳሌትነት መግለጽ፣
2ኛ. በወጣትነት ጊዜ ፈጣሪን ማስታወስ እንደሚገባ መቀስቀስ፣
3ኛ. የጥምቀት በዓልን አስፈላጊነት መግለጽ፣
4ኛ. ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ያለን ልዩነትና ጥላቻ ማሳየት፣
5ኛ. የመንግሥትን ወቅታዊ አሠራሮችና ፖሊሲዎች መቃወም፣ የሚሉት ናቸው።

እነዚህ 5ቱም ያጠቃቀም ዘውጎች፣ ሙያን ወይም ተግባርን መሠረት አድርገው የተከፋፈሉ ስለሆኑ፣ ዘውግ ምደባው መሠረት ያደረገው ይዘትን (Content) ነው ማለት ይቻላል። በርግጥ በይዘት ቢለያዩም፣ የሚጋሩት አንድ እውነታም ጎልቶ የወጣ ይመስላል። ይኸውም፣ 5ቱም ዘውጋዊ መንገዶች፣ ልዩነትን እና/ወይም ማፈንገጥን የሚያቀነቅኑ መሆናቸው ነው።

[33] ቤናሞጽ (Ben Amos 1993: 209) ማሊኖውስኪን (Malinowski 1946 [1923]: 307) ጠቅሰው፣ እንደጠቆሙት፣ ማሊኖውስኪ፣ በነገረ ሰብ (anthropology) የሙያ መስክ ውስጥ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብን ሲያቀነቅኑ፣ የባህል ዐውድን እና የሁኔታ ዐውድን አውስተዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ምርምራቸው፣ ትኩረቱን ከ "ማኅበረሰብ" ወደ "ትርጉም" በማድረግ፣ በኋላ ላይ ፎክሎረኞች ላነሱት ዐውዳዊ ትንታኔ ፍንጭ እንደሆናቸው የመስኩ ምሁራን መስክረዋል ማለታቸውን ያገናዝቧል፡፡

በማፈንገጣቸው ውስጥ ሁሉንም ዘውጎች ያስተሳሰረ አንድ ቀጭን ክር ለመምዘዝ ከተሞከረ፣ ውሉ ከ5ኛው ዘውግ/ምድብ ("የመንግሥትን ወቅታዊ አሠራሮችና ፖለሲዎች መቃወም") ጋራ ተቋጥሮ ይገኛል ማለት ይቻላል። እናም፣ የተወሰኑ ማስረጃዎች ነቅሰን እያንዳንዱን ያጠቃቀም መንገድ (ዘውግ) እንደሚከተለው ለመተንተን ብሎም ለመፈከር ተችሏል።

### 4.1. የመጡበትን አካባቢ በአድባራቱ ስም ተምሳሌትነት መግለጽ

የጥምቀት ተመላሾች፣ በክብረ በዓሉ ላይ የየትኛው አጥቢያ፣ ሰፈር እና/ወይም ማኅበር ወዘተ. ሀገረሰባዊ ቡድን አባል እንደሆኑ ለመግለጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ዲያቆን ዳንኤል ሰይፈሚካኤል ይናገራሉ። እንደተባለው ወጣቶቹ ሰፈራቸው፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው፣ አካባቢያቸው ሲደርሱ ድምጻቸውን ጎላ አድርገው እንደሚዘምሩ፣ እልልታና ጭፈራውን እንደሚያደምቁት አጥኚውም በተደጋጋሚ ተመልክቷል።

የሕሊና (2010፡82) ጥናትም፣ የጥምቀት ተመላሾቹ "ከየት ሰፈር የትኛው ቅያስ የመጡ እንደሆነ የሚያመላክት ተመሳሳይ ልብሶችን አሠርተዋል፡፡ ለመጡበት ማህበራዊ ቡድን አምባሳደር መሆናቸውን በልዩ ልዩ መንገድ አስመስክረዋል፡፡ ይሄ ማህበራዊ ትስስርም የሚፈልቀው ከመጡበት መንደር ባህላዊና ማህበራዊ ተራክቦዎች ነው" እንዲል፣ ወጣቶቹ የሰፈራቸውን ወይም የአከባቢያቸውን ደብር ለመግለጽ፣ የአካባቢውን የቤተክርስቲያን ስም የሚያመለክት ጥቅስ መጠቀሙን ሊቀጥሉበት እንደሚችሉ መጠርጠር፣ ምክንያታዊ ነው ማለት ይቻላል። ለምሳሌ፣ "እኔ ከእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ" (ሉቃ.1÷19) የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ ያለበት ከናቴራ ያደረጉ የጥምቀት ተመላሾች ያጀቧቸው ሀገረሰባዊ ቡድኖች፣ በብዛት ከግቢ ገብርኤል አካባቢ ተነስተው፣ በቤተ መንግሥቱ አቅጣጫ ወደ ጃንሜዳ እየመጡ ታይተዋል (ጥር 10 ቀን 2004ዓ.ም.)።

እዚህ ላይ፣ የጥቅሱን ድምፀትና ሥነ ልሳናዊ አቀራረብ ለማጤን መሞከር፣ የጥምቀት ተመላሾችን ልዩነት የመፍጠር አካሂያድ ወይም አፈንጋጭነት፣ በተራዛሚውም ቢሆን የሚያመላክት ይመስላል። "እራስህን ከፍ ከፍ አታድረግ... ግብዝ አትሁኑ..." የሚል ቀኖናን አጥብቃ የምታቀነቅንን ሃይማኖታዊ ተቋም (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) "እንከተላለን" የሚሉት ወጣቶች፣ በከናቴራቸው ፊትና ኋላ ላይ አትመው፣ ያውም፣ በአንደኛ መደብ "እኔ" ብሎ የሚጀምር ጥቅስ ለበሰው ሲንቀሳቀሱ፣ ቢያንስ ዐይን ውስጥ ሊከታቸው እንደሚችል መገመት አያቅታቸውም። እውነታው ግን፣ "ልታይ ልታይ" ማለትን፣ "ከንቱ ግብዝነትን" አጥብቃ ከምታነውረዉ ቤተ ክርስቲያን፣ ከሃይማኖታዊ አስተምህሮዋም በተቃረነ መልኩ፣ "እዩኝ እዩኝ" ማለቱን፣ በአንዳች ነገር ጎልተው መታየቱን ወይም ዐይን ውስጥ መግባቱን እነርሱም አጥብቀው የሚፈልጉት መሆኑ ነው፡፡ በርግጥም፣ ይህን በማድረጋቸው ሊያስተላልፉ የሚፈልጉት መልዕክት[34] ነበረ ማለት ይቻላል፡፡

[34] ወጣቶቹ፣ በብዙ ጥረት ይሄንኑ አፈንጋጭነታቸው የሚያመላክት ጥቅስ ለማግኘት ይጥራሉ፡፡ የሚፈልጉትን ጥቅሶች ለማግኘት ብዙ የሃይማኖት ሊቃውንት እንደሚጠይቁም ዲያቆን ዳንኤል ክብረት የራሳቸውን ገጠመኝ መሠረት አድርገው ለአጥኚው ገልጸዋል (ጥር 19 ቀን 2004 ዓ.ም.)።

በሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ የሚኖሩ የአንድ ሰፈር የጥምቀት ተመላሾች፣ "ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ" (ራእ. 12÷7) የሚለውን ጥቅስ በከናቴራቸው አትመው ሲሄዱ፣ ጥቅሱ አጥቢያቸውን ከመግለጽ ያለፈ ሌላ ሚና እንዳለው አስቀድሞ መጠርጠር ትንሽ ከበድ ቢልም፣ የወቅቱን ሀገራዊ ዐውድ ያስተዋለ ግን፣ ብዙዎቹ የቡድኖቹ እንቅስቃሴዎች ባዕድ ላይሆኑበት ይችላሉ፡፡ "ዘንዶው" ከእማሪያው ፍቺ የዘለለ፣ ፍካሬያዊ ትርጉም እንዳለው የሚገባን ወጣቶቹ፣ ከሙስሊም ሱቆች ጋ ሲደርሱ ወይም ደግሞ፣ የፌደራል ፖሊስ ሲመለከቱ የሚሆኑትን ነገር ስናስተውል ነው፤ ጥቅሱን አጨኽው ሲናገሩት/ሲያነቡት፣ ወይም በመዝሙር መልክ ሊያቀነቅኑ ሲሞክሩት ወዘተ. ይታያሉና፡፡ ለምሳሌ፣ ብዙዎቹ መጥምቃዊያን (የተባለውን ጥቅስ ያደረጉትን ጨምሮ) ስድስት ኪሎ አንበሳ ጊቢ ፊት ለፊት ይገኝ ከነበረ የፖሊስ ጣቢያ ጋ ሲደርሱና በዙሪያቸው የፌዴራል ፖሊሶች እንዳሉ ሲመለከቱ፣

> " አንመካም በጉልበታችን፣
> እግዚአብሔር ነው የኛ ኃይላችን"

በማለት እየጮኹ ይዘምራሉ፡፡ በመካከል አንዳንዶቹ የሌላውን የከናቴራ ጥቅስ በተለየ ድምፀትና ኃይል፣ "ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ!" ወይም "ነፍሴን ከሰይፍ አድናት፣ ብቻነቴንም ከውሾች እጅ" (መዝ. 21÷20) በማለት ያነባሉ-ያነበንባሉ። እነ "ዘንዶ" እና "ውሾች" በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካላቸው ዐውዳዊ ትርጓሜ ባለፈ፣ ለሌላ ስሜት መግለጫነት ("ለመስደብያነት") የሚያገለግሉ ትዕምርቶች[35] እና/ወይም ተምሳሌቶች መሆናቸውን ለመረዳት የጥምቀት ተመላሾቹን ከዋኔ፣ ከሌሎች ሁኔታዊ ዐውዶች ጋራ እያናበቡ መመርመርን[36] ይጠይቃል፡፡ ለምሳሌ፣ ከምርጫ 97 በኋላ፣ አብዛኞቹ የአዲስ አበባ ወጣቶች፣ በፌድራል ፖሊስ እና በአጋዚ ጦር ላይ ከረር ያለ ጥላቻና ቁርሾ እንዳለባቸው ይነገራል (ልደቱ 2002)፡፡ በወቅቱ አጥኚው ያገኛቸው የነበሩ፣ የሚያውቃቸውና ያስተማራቸው ወጣቶች በፌደድራል ፖሊሶችና በአጋዚ ወታደሮች ላይ ቀላል የማይባል ጥላቻና ሥጋት እንደነበረባቸው ያስታውሳል፡፡

በጥምቀት ክብረ በዓል የጥምቀት ተመላሾቹ የፌደራል ፖሊሶቹን ሲያዩ፣ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ፤ አንድም ጥላቻቸውን፣ አንድም ፍራቻቸውን የሚያስተጋባ ነበረ፤ በቻሉት ልክ ሲጯጯሁም፣ ሲገጫጩም የነበሩ ሀገረሰባዊ ቡድኖች ታይተዋል፡፡ በዚያው ጊዜ፣ ከፖሊስ

---

[35] በዚህ ጥናት ነገረ ትዕምርት (semiotics)፣ ነገረ ተምሳሌትንም ይመለከታል፡፡ የዶርሰን ጥናት፣ (Dorson 1972) ተምሳሌቶችን ከፎክሎር ዘውጎች አንዱ ከሆነው ከቁሳዊ ፎክሎር ጋራ መጠናት እንደሚችሉ መጠቆሙን፣ የቱርነር (Turner 1961) ጥናት ደግሞ ተምሳሌቶች የማኅበረሰብን ዕውቀት በውስጣቸው የያዙ ነገሮችን እንደሚወክሉ፣ በቅርጽም ይሁን በይዘት ማኅበረ ባህላዊ ፍቺ ጭምር ሊኖራቸው እንደሚችሉና አካላዊ ብቻም ሳይሆን ረቂቅ ነገሮችንም ስለሚወክሉ፣ ተጨባጭና ረቂቅ ተብለው በሁለት መልኩ ሊታዩ እንደሚችሉ ማስረዳቱን ያስታውሷል፡፡ ቱርነር (Turner 1967) በዛሚቢያ የንደንቡ ማኅበረሰብ ላይ ባደረጉት ጥናት ደግሞ ተምሳሌቶች፣ ቁሳዊ ጉዳዮች ብቻ እንዳልሆኑ ይልቁንም የማኅበራዊ ግንኙነት መዋቅሮች፣ ሁነቶች፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎች፣ ሥፍራዎች ጭምር ተምሳሌታዊ ሙያ ያላቸው መሆኑን አስረድተዋል፤ በቁጥሮች፣ በስሞች፣ በቀለሞች፣ በአቅጣጫዎች፣ በክስተቶች እና በቦታዎች የሚገለጽ ዐውዳዊ ትርጓሜ እንደሚፈከርባቸውም አብራርተዋል (ገዛኸኝ 2011)።

[36] ለዚህ ነው፣ ከወኔንና ዐውድን ሳይጨምር የአሀዶችን ፈሮች (patterns) ብቻ ማንፀሪያው አድርጎ የሚያስተነትነው የሌቪ ስትራውስ መዋቅራዊ ንድፈ ሐሳብ (Structural theory) ብቻውን፣ ለፎክሎር ምርምር ማንጸሪያ ማድረግ የሚመከር አይደለም ማለት የምንችለው፡፡

ጣቢያዉ ጎን፣ ከአንበሳ ግቢ ፊት ለፊት በሚገኘው "የኃይሉ ሥጋ ቤት" በረዳ ላይ ቁጭ ብለው ድራፍት እየጠጡ ይጨዋወቱ የነበሩ የጥምቀት ተመላሾች፣ ስለ ፌድራል ፖሊስና ስለ አጋዚ ወታደሮች ለአጥኚው ያወሩለት ቀልዶች፣ ወጣቶቹ ስለ 2ቱ የፀጥታ ተቋማት ያላቸውን አመለካከትና ሥነ ልቡናዊ ጫና የሚያንጸባርቁ ይመስላል፡፡ አጥኚው፣ ቀልዶቹ ከቀረቡበት ሁኔታዊ ዐውዶችና በኢትዮጵያ ላይ የረበበባት ከሚመስለው የዘመኑ መንፈስ[37] (zeitgeist) ጋራ እያግባባና እያጋባ ስላደመጣቸው ይሆን ወይም ሌላ? ብቻ ቀልዶቹ፣ የወቅቱን የወጣቶች ስሜትና አመለካከት ማንጸባረቅ ችለዋል ብሎ ያምናል፡፡ ከሰማቸው ቀልዶች መካከል 2ቱን እንደሚከተለው አሳጥሮ አቅርቧቸዋል፤

1. የፌደራል ፖሊሶች የውጭ ሀገር ቴሌቪዥን እየተከታተሉ እያለ፣ የአንድ የአውሮፓ ሀገር ተማሪዎቹ አምፀው፣ ድንጋይና ተቀጣጣይ ነገር ወደ ፖሊሶች እየወረወሩ ከተማዋን ቀውጢ ቢያደርጉም፣ ፖሊሶቹ ግን እራሳቸውን እየተከላከሉ አድመኞቹን በውሃ ለመበተን ሲራወጡ ታይተዋልና ሁኔታው ግራ ያጋባው አንዱ የፌደራል ፖሊስ፣ "የሚረጩት ምንድን ነው?" ብሎ ሲጠይቅ አሰልጣኙ፣ ፈጠን ብሎ "ውኃ" መሆኑን ነገረው... ወዲያው ፖሊሱም ‹ነገሩ ገብቶኛል› በሚመስል ዓይነት ራሱን እየነቀነቀ፣ "አሃ! ውሃው የፈላ ነው ማለት ነው..." ብሎ አረፈው፡፡

2. የአፍሪካ መሪዎች በሶማሊያ ጉዳይ ለመምከር ወደ አፍሪካ ኮሚሽን አድራሻ ሲሄዱ፣ አንዲት አህያ መሀል አስፋልት ላይ ቆማ አላሳልፋቸው አለች፡፡ እየደጋገሙ የመኪና ጡሩንባቸውን ቢያናፉ፣ ምንም አልመስል አላት፡፡ ስለ ሁኔታው ለጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ተደውሎ ተነገራቸውና በፍጥነት ደረሱ፡፡ እሳቸው እየደጋገሙ የመኪናውን ጥሩንባ ቢለቁባት፣ "አህያዋ ወይ ፍንክች የአባ ቢላዋ ልጅ!" አለች፡፡ ነገረ ሁኔታዋ ያስፈራቸው መለስ፣ ከመኪናቸው ወርደው ወደ አህያዋ ተጠጉና በጆሮዋ፣ "አውቄብሻለሁ! ‹ግንቦት ሰባት› የላከሽ ነሽ አይደል!? አጋዚ መጥቶ ይገላግልኛል... ይሄው እንደውም፣ ፌደራል ፖሊስ መጣልሽ!" ሲሏት አራት እግሯን አንስታ ፈረጠጠች፡፡

የጥምቀት ተመላሾቹ፣ በወቅቱ ፖለቲካዊ ተልዕኮም የነበራቸው አንዳንድ የአጋዚ ወታደሮችና የፌደራል ፖሊሦች፤ "... ርህራሄ የሚባል ያልፈጠረባቸው፣ ከልክ ያለፉ ጨካኞችና አረመኔዎች ናቸው... እንኳን እኛን አባ! የሸገር ልጆችን ቀርቶ፣ ደመነፍሳዊ የሆኑ እንስሳትን እንኳ ኢያምኑማ! ግንቦት ሰባት! አሸባሪ! ምናም እያሉ... ሸቤ አስገብተው ይዘለዝሉሃል! ፍሬንድ! ..."[38] በማለት አንዳንድ የፀጥታ ተቋማቱ አባላት፣ የሰብእና መንጠፍ (dehumanization) የተጠናወታቸው እንደነበሩ ለአጥኚው አጫውተውታል፡፡ እዚህ ላይ፣ የጥምቀት ተመላሾቹ የመጽሐፍ ቅዱስ

[37] "ጽንሰ ሐሳቡ በዋናነት በተወሰነ ዘመን ውስጥ የተከናወኑና የሆኑ ነገሮችን፣ ራሳቸውን ሳይሆን ነገሮቹ በሰው ልቡና ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ ይመለከታል" (ቴዎድሮስ 2001፡265)፡፡

[38] ይህን የታዳሚ አስተያየት (Commentary) የተናገረው፣ የፈረንሳይ ሰፈር ሀገረሰባዊ ቡድን አባል የነበረ የ26 ዓመት ወጣት ሲሆን፣ "... ምንም ነገር አላውቅም ነበር... በምርጫ 97 ወቅት ምንም ሳላደርግ! የፌደራል ፖሊስ፣ ታላላቆቼ ከሆኑ የሰፈሬ ጎረምሶች ጋር አብሬ ተጋፍፌ፣ በሸዋ ሮቢት እስር ቤት ለሦስት ወር ታስሬ ስቀጠቀጠጥ ነበረ..." በማለት ጉልበቱ ላይ ያለውን ጠባሳ እንዳሳየው፣ አጥኚው ያስታውሳል (ጥር 10 ቀን 2004 ዓ.ም.)፡፡

ጥቅሶቹን፣ ከሃይማኖታዊ ተቋሟ አስተምህሮዎች በተለየ ሁኔታ፣ የሀገረሰባዊ ቡድኑን ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም ማቀንቀኛ የትግል መሣሪያ አደረጓቸው እንዴ? የሚል ጥያቄ ሁሉ ሊጫርብን ይችላል (አባሪ "መ" ላይ፣ በተራ ቁጥር 4፣ 8፣ 7፣ 9 እና 11 የተዘረዘሩ ጥቅሶች፣ በዚህ የጥቅስ አጠቃቀም ዘውግ ሥር የሚመደቡ ናቸው)።

## 4.2. በወጣትነት ጊዜ ፈጣሪን ማስታወስ እንደሚገባ መግለጽ

የጥምቀት ተመላሾች፣ በወጣትነት ጊዜያቸው ፈጣሪያቸውን (እግዚአብሔርን) ማሰብ፣ ለፍቅሩ መገዛት፣ ለክብሩ መውደቅ... እንደሚገባ ለማሳሰብና ቀኖናውን ለማጽናት ሲሉ፣ 4 ያህል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በተደጋጋሚ ተጠቅመዋል። ለምሳሌ፣ መጽሐፈ መክብብ ምዕራፍ 12 ቁጥር 1 ላይ፣ "የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ" እና ማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ቁጥር 3 ላይ፣ "የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውን ሁሉ አቅኑ" ("እኛ የዓለም ብርሃን ነን!" የሚል አባባልም አስከትሏል) የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል።

ወጣቶቹ፣ "የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ" የሚለውን ጥቅስ ባልንጀሮቻቸውን በእነሱ ጎራ ለማሳለፍ እንደሚጠቀሙበት አጥኚው ተመልክቷል፡፡ በርግጥ፣ በፌዝ ("በቶገራ") መልክ፣ "በርጫ ከምትቀጨቅጭ ሚኪን አትሸኝም... በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን እንጂ ችክህን[39] አታስብ ይላል መጽሐፉ"[40]ዓይነት አባባሎችም ሲነገሩ ይሰማል። እዚህ ላይ ወጣቶቹ፣ በቀልድም ሆነ በምር ባልንጀሮቻቸውን ለመቀስቀስ፣ ወደ እነርሱ ጎራ ለመቀላቀል ጥቅሱን እንደተጠቀሙበት ወይም እንደተገለገሉበት ታይቷል ለማለት ነው (አባሪ "መ" በተራ ቁጥር 6፣ 16፣ 18 እና 19 ላይ የተዘረዘሩ ጥቅሶች፣ በዚህ የጥቅስ አጠቃቀም ዘውግ ሥር የሚመደቡ ናቸው)።

## 4.3. የጥምቀት በዓልን አስፈላጊነት መግለጽ

የጥምቀት ተመላሾቹ በከናቴራቸውና በባነሮቻቸው ላይ ካሰፈሯቸውና በአጥኚው ከተመዘገቡ 40 ጥቅሶች ውስጥ 11 ያህሉ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የጥምቀትን በዓል አስፈላጊነት፣ ክብርና ሞገስ ይገልጻሉ። አባሪ "መ" ላይ ከተዘረዘሩት ጥቅሶች መካከል ለምሳሌ፡- "ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል" (ማር. 16÷16)፣ "ሕዝቡን የአምላካችሁን የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ሌዋዊያን ካህናት ተሸክመው ባያችሁ ጊዜ ከሰፈራችሁ ተነስታችሁ ተከተሉት" (ኢያ. 3÷3) የሚሉትን ሁለት ጥቅሶች ብንመለከት የጥምቀትን አስፈላጊነትና ከየሰፈሩ እየተነሱ በክብር ሊሸኙት እንደሚገባ ይጠቁማሉ።

ጥቅሶቹ፣ የጥምቀትን በዓል የሚዘክሩ ቢሆኑም፣ ጥምቀት ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት ቀኖና አንጻር ብቻ ከመግለጽ ይልቅ፣ ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋራ ያለውን ልዩነት በማጉላት፣ የራስን ሃይማኖት

[39] "የሴት ጋደኛን" ወይም ሴት ፍቅረኛን የሚወክል "የአራዳ ቃል" ነው፡፡

[40] በጥር 10 ቀን 2004 ዓ.ም. ምሳ ሰዓት አካባቢ ታዲዮስ የተባለ የአጥኚው ሰፈር ወጣት፣ የቢላ "መጥምቃውያን፣" ጓደኛውን ሲቀልድ ሰምቶ፣ በማስታወሻው የመዘገበው አሀድ (text) ነው፡፡

አዳኝነት፣ ትክክለኝነት መግለጽ ላይ ትኩረት መደረጉን ማሳየት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡- “*ያመነ የተጠመቀ ይድናል*” የሚለው ጥቅስ፣ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ከሌሎች በተለይ በጥምቀት ከማያምነው ከእስልምና ሃይማኖት ዋነኛ መለያ ቀኖናዎች መካከል አንዱ እንደሆነ ይነገራል (ኢኦተቤ. 2000)፡፡ ቀደም ሲል እንደተመላከተው የጥምቀት ተመላሾቹ ታቦቱን ሲሸኙ፣ በሙስሊም ሱቆች፣ በየሰፈሩ ካሉ የሙስሊም መስገጃ ዛውያዎች አቅራቢያ ሲደርሱ ወይም በዚያ ሲያልፉ፣ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው፣ እየዘመሩት የነበረውን የጥምቀት መዝሙር ደመቅ አድርገው ሲዘምሩ፣ “*ያመነ የተጠመቀም ይድናል! … ያላመነ ይፈረድበታል!*” እያሉ በዝማሬያቸው መካከል ጥቅሱን አጩኸው ሲያስተጋቡም ታይቷል፡፡

በሌላ በኩል፣ ሁኔታዊ ዐውዶቹን ላስተዋለ፣ አንዳንድ ሀገረሰባዊ ቡድኖች፣ “እንደኛ ተጠምቃችሁ ተፈወሱ፤ ካልሆነ እንጦሮጦስ ትወርዳላችሁ” የሚል ዓይነት መልእክት በስሜት ማስተላለፍ የፈለጉ ሊመስለውም ይችላል፡፡ እዚህ ላይ፣ ከአንደኛው የወጣቶቹ ማኅበራዊ ቡድን አልባሳትና ባነር ላይ “እኛ የዓለም ብርሃን ነን!” የሚል የ*መጽሐፍ ቅዱስ* ምዕራፍና ቁጥር ያልተጠቀሰበት፣ በራሳቸው ያዋቀሩት የሚመስል ጥቅስም “አጩኸው” ሲያስተጋቡ ማጋጠሙን ያጤኗል (በአባሪ “መ” ውስጥ በተራ ቁጥር 10፣ 15፣ 17 እና ከ21-28 የተዘተዘሩት ጥቅሶች በዚህ ክፍል ወይም በዚህ የጥቅስ አጠቃቀም ዘውግ ሥር ይመደባሉ)።

## 4.4. ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋራ ያለን ልዩነት ማሳየት

በጥናቱ ከተሰበሰቡ 40 ጥቅሶች መካከል 14ቱ፣ በዚህ የጥቅስ አጠቃቀም ዘውግ ሥር ተመድበው ሊተነተኑ የሚችሉ ናቸው። ብዙዎቹ ጥቅሶች ከእስልምና እምነት ጋራ ያለውን ልዩነት የሚያፀኑ፣ የእስልምና እምነት ተከታዮችን ለማሸማቀቅና ለመዝለፍ ሁሉ የሚውሉ እንደሆኑ፣ የዚህ ጥናት አቅራቢ በተለያዩ ዐውዶች ላይ ታዝቧል፡፡ ለምሳሌ፣ በመጀመሪያው ንዑስ ክፍል የቀረበውን ትንታኔ ያስታውሷል።

የጥምቀት ተመላሾችን ማንነት በሚያስቃኘው ቀዳሚዉ ክፍል ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ “ቁጡ ሐዋርያቱ” ለመጀመሪያ ጊዜ በ2000 ዓ.ም. ወደ ጥምቀት ክብረ በዓል እንዲመጡ ምክንያት ከሆኑት ውስጥ የአክራሪ ሙስሊሞች እንቅስቃሴ እንደነበር ማስረጃዎቹ ያመላክታሉ፡፡ በከናቴራዎቻቸው ላይ የተጠቀሱት አብዛኞቹ ጥቅሶች እስልምና ሃይማኖት ላይ ማነጣጠራቸውም፣ ከአነሳሳቸው ጋር ተጠየቂያዊ ዝምድና ያለው ይመስላል። በዚህ ክፍል ሊተነተኑ ከሚችሉ ጥቅሶች መካከል፣ “ብዙ ወሾች ከብበውኛልና የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ” (መዝ 22÷16) እና “እግዚአብሔር ተዋጊ ነው፣ ስሙ እግዚአብሔር ነው” (ዘጸ. 15÷ 3) የሚሉትን ብናይ፣ በየጥምቀት ተመላሾቹ አልባሳትና ባነሮች ላይ የሚጮኽ ድምፀት እንደሚስተጋባባቸው መገመት አይከብድም፡፡

የጥምቀት ተመላሾችም፣ ይህን ጩኸት (ተዋጊነት) ከእስልምና ሃይማኖት “የጂሃድ አዋጅ” ጋር በትይዩ ያቀረቡት የአጸፋ ምላሽ ይመስላል፡፡ የምርምሩ ተሳታፊዎችም፣ ተመሳሳይ ሐሳብ እንዳላቸው ገልፀዋል። እነዚህ ተናዳፊና ተንኳሽ ጥቅሶች በተለያዩ ቁሶቻቸው ላይ ማሳተማቸውን

ብቻ ሳይሆን፣ ድፍረት የተሞላበት እንቅስቃሴያቸውንም ታዝበው ይመስላል፣ የምርምሩ ተሳታፊዎች፣ "ቁጡ ሐዋርያት" እያሉ እስከ መጥራት መድረሳቸው ይታወሳል (በአባሪ "መ" በተራ ቁጥር 3 ፣ 5፣ 12፣ 13 ፣14 ፣ 20 ፣ 24 ፣ 30 ፣ 31 ፣ 32 ፣ 33 ፣ 34 እና 36 የተዘተዘሩት ጥቅሶች በዚህ ክፍል ወይም በዚህ ዘውግ ሥር ይመደባሉ)።

#### 4.5. በመንግሥት ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ማንጸባረቅ

በዚህ ክፍል የሚመደቡት ጥቅሶች፣ ከመንግሥት ወቅታዊ ተግባራት ጋራ (በአብዛኛው ከ2002 እስከ 2004 ዓ.ም. የታህሳስ ወር ድረስ ከወሰናቸው ጉዳዮች ጋራ) የቅርብም የሩቅም ግንኙነት ያላቸው ይመስላሉ፡፡ መንግሥት በዚያው ሰሞን ከወሰዳቸው እርምጃዎች ጋራ የሚቆራኙ ጥቅሶች ይበዘባቸዋል። ቀደም ሲል በሌሎቹ ክፍሎች ለተነሱ ችግሮች ለምሳሌ፣ "አክራሪ ሙስሊሞች" እንዲፈጠሩ በማድረግ፣ ፌዴራል ፖሊሶችን አሰማርቶ በማስፋራት ወዘተ. መንግሥት ተጠያቂ እንደሆነ በግልጽና በድፍረት የሚናገሩ ጥቂት ወጣቶች ወይም "ቁጡ ሐዋርያት" እንደነበሩ ጥናቱ አመላክቷል።

የምርምር ተሳታፊዎቹ፣ መንግሥትን በደፍረት በፊት ለፊት ከመቃወም ይልቅ ሌሎች ቀዳሚ መከለያዎችን ወይም ሽፋኖችን በመጠቀም፣ ስሜታቸውን ለመግለጽ ጥረት የሚያደረጉ ቡድኖች በሁሉ የሃይማኖት ተቋማት ሥር ከማቆጥቆጥ አልፈው እየፋፉ እንደነበረ ገልጸዋል። እንደ ሽፋንነት ለመጠቀም ደግሞ ሃይማኖት ተመራጭ እንደሆነችም ተናግረዋል፡፡ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትም፣ "መንግሥት፣ በአንድ በኩል ሕገመንግሥቱ በሃይማኖት ላይ ጣልቃ እንዳይገባ ስለሚከለክለው፣ በሌላ በኩል ሃይማኖት የሚባለው ነገር በጣም ሴንሴቲቪ እየሆነ በመምጣቱ ሳቢያ ወደኋላ ሲል በመታየቱ፣ ብዙዎች ሃይማኖትን ሽፋን እያደረጉ የተለያዩ ስሜቶቻቸውን በተደራጀ መንገድ እያስተጋቡ ነው..." በማለት ማስረዳታቸውን ያስታውሷል።

ቀደም ሲል፣ በመጀመሪያው የጥቅስ አጠቃቀም ዘውግ ላይ፣ "የጥምቀት ተመላሾቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶቹን፣ ከሃይማኖታዊ ተቋሚ አስተምህሮዎች በተለየ ሁኔታ፣ የህገረሰባዊ ቡድኑን ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም ማቀንቀኛ የትግል መሣሪያ አደረጓቸው እንዴ?" የሚል ጥያቄ እንደተጫረብን መጠቆማችን፣ ምክንያታዊ ነበረ ማለት ይቻላል፡፡ እዚህ ላይም፣ ወጣቶቹ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶቹን እንደ ፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ማሰራጫ የትግል መሣሪያ መጠቀማቸውን መተንተን ይቻላል። ለምሳሌ፣ መጽሐፈ ነገስት ቀዳማይ ምዕራፍ 20፣ ቁጥር 19 ላይ፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል- ገድለህ ወረስኸውን? ብለህ ንገረው" እና "ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ስፍራ የአንተን ደም ደግሞ ውሾች ይልሱታል" የሚሉ ጥቅሶችን ብንመለከት የጥምቀት ተመላሾቹ ለምን ዓላማ ጥቅሶቹን እንደተገለገሉባቸ የሚገባን፣ ጥቅሶቹን ከወጡበት የመጽሐፍ ቅዱስ ዐውድ ወስጥ አናበን ካየናቸው ነው።

ጥቅሶቹ የተወሰዱት ከመጽሐፍ ነገስ ቀዳማይ፣ ምዕራፍ 20 ውስጥ ነው። ይህን ጥቅስ፣ ሙሉ ምዕራፉን ስናነበው እሥራኤላዊው ናቡቴ የሰማርያ ንጉሥ፣ አክዓብ የወይን ቦታውን እንዲሸጥለት ቢጠይቀውም፣ "ናቡቴ የአባቶቼን እርስት አልሸጥልህም" (፩ኛ ነገ. 20÷ 9) ብሎ እንደመለሰለትና

ንጉሥ አክዓብም ምትክ ሌላ መሬት እሰጥሃለው ቢለውም፣ ናቡቴ በጄ ባለማለቱ ተናዶ እንደታመመ ተገልጿል። በኋላም፣ በንጉሡ ሚስት በኤልዛቤል ትዕዛዝ፣ እግዚአብሔርን ተሳድቧል በሚል በሐሰተኛ ክስ እራሳቸው ከስሰውና እራሳቸው መስክረው፣ ናቡቴን ተቀጥቅጦ እንዲገደል አድርገው የወይን ቦታውንም እንደወረሱና እግዚአብሔር በኤልያስ ላይ አድሮ፣ "አክዓብን ንገረው... እግዚአብሔር እንዲህ ይላል- ገድለህ ወረስኸውን ብለህ ንገረው። ደግሞ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል- ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ስፍራ የአንተን ደም ደግሞ ውሾች ይልሱታል ብለህ ንገረው" (፩ኛ ነገ. 20÷19) እንዳለውና እግዚአብሔር የእጃቸውን እንዲያገኙ እንደፈረደ ታሪኩ ይናገራል።

እዚህ ላይ፣ የጥምቀት ተመላሾች እነዚህን ጥቅሶች ለምን እንደተጠቀሙባቸው፣ ቀድሞ መገመት ይከብድ፣ ግራም ያጋባ እንደ ነበር ያስታውሷል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን ስናነብ ግን፣ በወቅታዊው የመንግሥት የመሬት ሊዝ አዋጅ ጋራ ተያይዞ በተለይ፣ "... የሊዝ አዋጁን በፓርላማ ካጸደቀ በኋላ፣ ሕዝቡ ይወያይበት በማለት ለፈጠረው ቀልድ፣ ባዲሳባ ሕዝብ ላይ ላሳየው ጥላቻና ንቀት... የተሰጠ ጠንካራ ተቃውሞ፣ ማስጠንቀቂያ ነው..." መባሉን ስንሰማ፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ* ጥቅስ፣ ለፖለቲካ ትግል መሣሪያ ሊጠቀሙበት እንደቻሉ፣ በተጨባጭ እንገነዘባለን። ናቡቴ በሐሰተኛ ጉዳይ ተከሶ፣ በሐሰተኞቹ በራሳቸው ተመስክሮ፣ በራሳቸው የተፈረደበትን ታሪክ ደግመን ስናነበው፣ መንግሥት፣ "የፀረ-ሽብር አዋጅ እራሱ አሳውጆ፣" ራሱ ከሶ፣ ራሱ መስክሮ፣ ራሱ እንደፈረደባቸው፣ እነ "አመንስቴ" ያወጡትን መግለጫ ሁሉ የሚያጠይቅ (justify የሚያደርግ) ነበር ማለት ይቻላል [በአንዳንድ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች እና የግል ጋዜጣና መጽሔት ጋዜጠኞች ላይ የተደረገ "እስርና ስቃይ"ን ያስታውሷል]።

በዚህ የዘውግ ማሕቀፍ ውስጥ በዚያው ሰሞን፣ 16ኛው ዓለም አቀፍ የኤካስ (ICASA) ጉባኤ በአዲስ አበባ ሲካሄድ፣ ኅዳር 23 ቀን 2004 ዓ.ም. 200 የሚሆኑ "ግብረሰዶማውያን" በአዲስ አበባ እንዲሰበሰቡ ("መንግሥት ሕገ መንግሥቱ ላይ ያወጣቸው አንቀጾች ሳይገድቡት") መፍቀዱ፣ የተለያዩ የሃይማኖት ተቋሞችንና ምእመኖቻቸውን አስከፍቶ ነበረ፡፡ የጥምቀት ተመላሾቹም፣ በጥምቀት ክብረ በዓላት ላይ፣ "በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያሉትን የሶዶማዊያን ቤቶች አፈረሰ" (፪ኛ ነገ. 23÷7) እና "ሁሉም እንደ ሰዶም የሚኖሩባትም እንደ ገሞራ ሆኑብኝ ኤር. 23÷14 ቅድስት ሆይ!" የሚሉ፣ ከበዓሉ መንፈስ ጋራ የማይሄዱ "ግብረሰዶም ተኮር" ጥቅሶችን እስከ ማጣቀስ ደርሰው ("ተገደው") እንደነበረ ታይቷል፡፡

የጥምቀት ተመላሾቹ፣ "ቅድስት ሆይ!" በሚሏት፣ ክርስትናንም እስልምናንም ቀድማ በተቀበለችና "የብዙ አማንያን መናኸርያ በሆነች ሀገራችን ላይ ግብረሰዶማውያን በይፋ፣ ያውም በመስቀል አደባባይ..." እንዲሰበሰቡ መደረጉ፣ በጣም አስከፍቷቸው እንደነበረና ከጥምቀት ክብረ በዓል በፊት በየሰፈራቸው፣ በየአጥቢያ ደብራቸው ቅሬታቸውን በተለያዩ መንገዶች ለማንጸባረቅ ሞክረው እንደነበረ አጥኚው፣ ከምርምር ተሳታፊዎቹ ቃለ መጠይቆች ለመገንዘብና ማስረጃዎቹን ለማመሳከር ችሏል፡፡ በሌላ በኩል፣ የወቅቱን የኑሮ ውድነትና የድኅነት ኑሮ የሚያጋልጡ፣ ጥቅሶች መኖራቸውም፣ በጥናቱ ተረጋግጧል (በአባሪ "መ" ውስጥ በተራ ቁጥር 1፣ 35፣ ከ37-40

የተዘረዘሩት ጥቅሶች፣ በዚህ ክፍል ወይም በዚህ የጥቅስ አጠቃቀም ዘውግ ሥር መመደባቸውን ልብ ይሏል)።

**5. መደምደምያ**

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ በዋናነት በአንድ በኩል በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የጥምቀት ተመላሾች ወይም የጥምቀት አድማቂ ወጣቶች እንዴት እንደተደራጁ፣ ወደዚህ ተግባር እንዴት እንደመጡ፣ የገንዘብ ምንጫቸው ምንና ማን እንደሆነ፣ በመንግሥትና በሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ምን ዓይነት ጫና እየፈጠሩ እንደነበረ፣ ምላሽ ለመስጠት ሞክሯል፡፡ በሌላ በኩል፣ የጥምቀት ተመላሾቹ ለበዓሉ ማድመቂያ በሚል በአልባሳታቸውና በባነሮቻቸው ላይ የሚጽፏቸው ጥቅሶች ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ፣ እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ምን መልክ እየያዙ እንደመጡ፣ አንድምታቸውም ምን እንደሆነ በተለያዩ ዐውዶቻቸው ማንጸሪያነት ለመፈከር ተሞክሯል። በዚህም በዋናነት ጥቅሶቹ፣ ከቤተክርስቲያኗ ቀኖናዎች ባፈነገጠ መልኩ ለወጣቶቹ የታመቀ የውስጥ ብሶት መተንፈሻ፣ የትግል መሣሪያ እንደሆኑ ታውቋል። በዚህ የጥምቀት በዓልን መሠረት ባደረገ የቅኝት ጥናት፣ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ፣ መንግሥታት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ፣ አዳዲስ የፎክሎር ዘውጎች (የባህል ገጽታዎች) እንዲፈጠሩ ምክንያት ይሆናሉ ወይ? የሚል መሪ የምርምር ጥያቄ ማርቀቅ እንደሚቻል ማመላከት ታስቧል።

## ማጣቀሻዎች


ልደቱ አያሌው፤ 2002፤ *መድሎት*፤ አዲስ አበባ፣ ፕሮግሬስ ማተሚያ ድርጅት።

ሒሊና ሰብስበው፤ 2010፤ "ዘመናዊነትእና ባይታወርነት በጃንሜዳ ሀርሞኒካ ቃል ግጥሞች አውዳዊ ክዋኔ" *ባህልን ማወቅና መጠበቅ ለሁለንተናዊ እድገት፤ የአራተኛው አገርአቀፍ የባህል አውደ ጥናት መድብል*፤ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ የባህል ማዕከል፣ ከገጽ 57-87፡፡

አሕመዲን ጀበል፤ 2004፤ "አትነሳም ወይ፣ አትነሳም ወይ! የግፍ አገዛዝ አይበቃህም ወይ?" *የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት* (ቀጽ 2 ቁጥር 16 ጥር 2004) ገጽ 21።

መስፍን ወልደማርያም፤ 2002፤ *አገቱኒ፡ ተምረን ወጣን*፤ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ሰይፉ መታፈሪያ፤ 1993 (እ.ኤ.አ.)፤ "የፎክሎር መዝገበ ቃላት ጥንቀራ ቅድመ ዝግጅት፤" *የኢትዮጵያ ጥናት መጽሔት*፤ ቅጽ 26፣ ቁጥር 1 ጁን 1993፤ ገጽ፡ 73-116፡፡

በላይ ግደይ፤ 1995፤ *አክሱም*፤ አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማከፋፈያ ኃ.የተ.የግ. ማኅበር፤ አክሱም መደብር፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፤ 2001፤ *በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ*፤ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

አበባው ይርጋ፤ 2006 (እ.ኤ.አ.)፤ "የጥምቀት በዓል፤ ምንነቱ፣ ማሕበረ-ባህላዊ ዐውዶቹና ፋይዳዎቹ፤" *የኢትዮጵያ ጥናት መጽሔት*፤ ቅጽ 39፣ ቁጥር 1-2 ጁን-ዲሴምበር 2006፤ ገጽ፡ 151-174፡፡

አባ ጎርጎርዮስ፤ 1994፤ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፤ አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ኢስሃቅ እሸቱ፤ "ለምን ትፈራለህ!?" *የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት* (ቀጽ 2 ቁጥር 16 ጥር 2004) ገጽ 16።

የሙስሊሞች ጉዳይ ፊቸር ጸሐፊ ቡድን፤ "1987ን እንደማስታወት" *የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት* (ቅጽ 2፣ ቁጥር 16፣ ጥር 2004) ገጽ 3።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ 1980፤ *መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*። ናይሮቢ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፤ 2000፤ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም. (2000)*፤ አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፤ *ሥርዓተ ጥምቀት*። አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1947።

ዮሐንስ ሰ.፤ "ሕዝብ ቆጠራ ጠቃሚ መረጃ ወይስ የፖለቲካ ቁማር?" *አዲስ አድማስ ጋዜጣ* (ቅጽ 8፣ ቁጥር 462፣ ኅዳር 27 ቀን 2001 ዓ.ም.) ገጽ 5።

ዘኤልያስ ወ/ሚካኤል፤ 2004፤ "በውዝግብ የተቋረጠው የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎች፤" *ዕንቁ* (4ኛ ዓመት፣ ቀጥር 068፤ ገጽ 16-17)፤ አዲስ አበባ፡ አፍሮ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ገዛኸኝ ጸጋው፤ 2011፤ "የወዳጃ ሀገረሰባዊ ዘውጎች ዐውዳዊ ፍካሬ በወሎ" በአ.አ.ዩ.፤ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለዶክትሬት ድግሪ ማሟያ የቀረበ።

.........፤ 2009፤ "ወዳጃ እና ንግሥና በወሎ" (የወሎ ዩኒቨርሲቲ፣ ጥር 6 ቀን 2009 ዓ.ም. ባዘጋጀው "የመጀመሪያው የባህል፣ የፎክሎርና የቋንቋ ሀገር አቀፍ አውደ ጥናት" ላይ የቀረበ)፤ ያልታተመ፡፡

ገዛኸኝ ፀ.፤ 2004፤ "በኢትዮጵያ ምክንያታዊና ነፃ ሐሳብ ሲመክን፣ ሃይማኖት መጠፋፊያ ይሆናል፤" *ዕንቁ* (4ኛ ዓመት፣ ቀጥር 068፤ ገጽ 16-17)፤ አዲስ አበባ፡ አፍሮ ማተሚያ ድርጅት፡፡

.........፤ 2001፤ "የሃይማኖት ነፃነት ያልገባቸው፣ የሃይማኖት ነፃ አውጪዎች፤" *አዲስ አድማስ ጋዜጣ* (ቅጽ 8፣ ቁጥር 470፣ ጥር 23 ቀን 2001 ዓ.ም.) ገጽ 3።

Bauman, Richard. 1986. "Context," In Richard Dorson, ed. *Hand book of American Folklore*. Indiana: Indian University Press.

...........1977. *Verbal Art as Performance*. Prospect Heights, N. Y.: Waveland Press.

Bell, Chatherine. 1997. *Ritual: Perspectives and Dimensions.* New York: Oxford University Press.

Ben-Amos, Dan. 2011. "Genre," In *Folklore: an Encyclopedia of Belief, Custom, Tales, Music, and Art*. (2th ed.). Barbara, California፡ ABC-CLIO, LLC, pp. 617-623.

………..1993. "Context in Context," In *Western Folklore*, Vol. 52, No. 2/4, Theorizing Folklore: Toward New Perspectives on the Politics of Culture, pp. 209-226.

Chaillot, Christine. 2002. The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church Tradition. Paris: Inter-Orthodox Dialogue.

Dorson, Richard M. 1972. "Current Theories of Folklore," In *Folklore and Folklife: An Introduction*. ed. Richard M. Dorson. Chicago: University of Chicago Press, pp. 7-50.

Eide, Øyvind. 2000. *Revolution & Religion in Ethiopia*. Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

Gray, David E.. 2004. *Doing Research in the Real World*. London: Sage Publications.

Huntington, Samuel P. 1996. *The Clash of Civilizations and the Remaking of World Order*. New York: Simon and Schuster.

Jason, Heda. 1997. "Texture, Text, and Context of the Folklore Text vs. Indexing," In *Journal of Folklore Research*. Vol. 34, No. 3 (Sep.-Dec.), pp. 221-225.

Levine, Donald Nathan. 2006. *Powers of the mind: the reinvention of liberal learning in America*. London፡ University of Chicago Press.

Oring, Elliott. (ed.). 1986. *Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction*. Logan: Utah State U.ity Press.

Orlowska, Izabela. 2009. "Performance and Ritual in Nineteenth-Century Ethiopian Political Culture," In *Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies.* ed. by Svein Ege, Harald Aspen, Birhanu Teferra and Shiferaw Bekele, Trondheim, pp. 75-83.

Schoemaker, George H. (ed.). 1990. *The Emergence of Folklore Everyday Life: A Field Guide and Source Book*. Bloomington, Indian: Trickster Press.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. 2005. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions*. Utah: Utah State University Press.

Toelken, Barre. 1996. *Dynamics of folklore*. Logan: Utah State Univ. Press.

## አባሪዎች

### አባሪ "ሀ" (የ2001 ዓ.ም. ጥቅሶች)

ከዚህ በታች የቀረቡት አባባሎች (ጥቅሶች)፣ በ2001 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ወጣቶች ከለበሷቸው ከናቲራዎች/ቲሸርቶች እና በሚኒባሶች ላይ ከተለጠፉ "ስቲከሮች" የተገኙ መሆናቸው ተገልጾ፣ *ለሐዲስ ሊድማስ ጋዜጣ*[41] ዝግጅት ክፍል ከተላከ ደብዳቤ የተወሰዱ ናቸው። ላኪው የእስልምና እምነት ተከታይ መሆኑን ገልፆ እንደነበር ያስታውሷል።

1. "ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት"
2. "ከኋላ የመጣ አይን አወጣ"
3. "ቅዱስ ገብርኤል እያለልኝ አህዛብን አልፈራም"
4. "ስምሽን እያነሱ የሚቀልዱ መናፍቃን ወዮላቸው! "
5. "አንድ ጥምቀት፣ አንደ ሃይማኖት አንድ ሀገር"
6. "የመጀመሪያዋን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት በማመኔ ኮራሁ"
7. "በጉብዝናህ ወራት ተዋህዶን ለምድ ከለበሱ ተኩላዎች ጠብቃት"
8. "ቅዱስ ገብርኤል እያለ አህዛብን አልፈራም"
9. "ካሃዲዎች በደጅሽ ይሥግዳሉ"

### አባሪ "ለ" (የ2002 ዓ.ም. ጥቅሶች)

ከዚህ በታች ከቀረቡት አባባሎች (ጥቅሶች) ከፊሎቹ፣ "በ2002 ዓ.ም. በአዲስ አበባ እና በአንዳንድ የሀገሪቱ ከተሞች የጥምቀት ክብረ በዓልን ለማክበር ከወጡ ወጣቶች ከናቲራ/ቲሸርት ላይ ታትመው እንደነበረ ተነግሯል፡፡" ከፊሎቹም፣ በማኅበረ ቅዱሳን *የስመጽድቅ ጋዜጣ* ከፍተኛ ሪፖርተር ከነበሩት ከዲያቆን ታደሰ ወርቁ ቃለ መጠይቅ[42] እና *ብዕር* (ቅጽ 1፣ ቁጥር 6፤ ሚያዚያ 2002 ዓ.ም.) ከተሰኘች መጽሔት ("የሙስሊም ልሳን") የተወሰዱ ናቸው።

1. "ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት!"
2. "አንድ ሃይማኖት አንድ ጥምቀት!"
3. "ኢትዮጵያ በድንግል ማርያም የተባረከች ሀገር ናት!"
4. "በማርያም በቅዱሳንና በመላይክት አማላጅነት እናምናለን!"
5. "ቅዱስ ሚካኤል ጣልቶቼን አሳፈራቸው!"
6. "ብዙ አባቶች የተሰውላትን ሃይማኖት እንጠብቃት!"
7. "መድኃኒዓለም አባቴ ሀገሬን ጠብቀልኝ!"
8. "የዓለም ብርሃን ነን!"
9. "አቡነ ጴጥሮስ የተሰውላት አንድ የተዋህዶ ሃይማኖት!"
10. "እኔ መልአክን በፊትህ እሰዳለሁ" (መዝ 22÷ 16)
11. "እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል÷ ወደ እሳትም ይጣላል" (ማቴ 3÷ 10)
12. "ያመነ የተጠመቀ ይድናል÷ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" (ማር. 16÷ 16)

---

[41] የጋዜጣው ከፍተኛ አዘጋጅ የሆኑት ሰለሞን ገብረ እግዚአብሔርና የዚህ ጥናት አቅራቢ ከወቅቱ ሁኔታ አንጻር ሃይማኖት ላይ ያነጣጠሩ ምርምራዊ መጣጥፎችን መጻፍችን ያመሳከሯል።

[42] ቃለ መጠይቁ የተደረገው፣ ጥር 21 ቀን 2004 ዓ.ም. (ከረፋዱ 4:10-6:50) አምስት ኪሎ አካባቢ፣ "ኩችና ካፌ" ይባል በነበረ (በአሁን ጊዜ በቦታው የማይገኝና የፈረሰ) ሻይ ቤት ውስጥ ነበረ፡፡

13. "የአመላካችሁን የእግዜአብሔርን ቃልኪዳን ታቦት ሌዋውያን ካህናት ተሸክመውት ባያችሁ ጊዜ ከሰፈራችሁ ተነስታችሁ ተከተሉት" (ኢያ. 3÷ 3)
14. "ነፍሴን ከሰይፍ አድናት÷ ብቻነቴንም ከውሾች እጅ" (ምዝ. 21÷ 20)
15. "የአህዛብ ነገዶች ሁሉ በፊትህ ይሰግዳሉ" (መዝ. 21÷27)

## አባሪ "ሐ" (የ2003 ዓ.ም. ጥቅሶች)

ከዚህ በታች የቀረቡት አባባሎች (ጥቅሶች) በ2003 ዓ.ም. በአዲስ አበባ እና በአንዳንድ የሀገሪቱ ከተሞች የጥምቀት ክብረ በዓልን ለማክበር ከወጡ የጥምቀት ተመላሾች ከናቲራዎች/ቲሸርቶች እንዲሁም ለየድንኳኖቻቸው እና መድረኮቻቸው ካሠሯቸው (ከሰቀሏቸው) "ባነሮች" ላይ ታትመው እንደነበረ፣ ከማኅበረ ቅዱሳን *የስመጽድቅ ጋዜጣ* ከፍተኛ ሪፖርተር ከወ/ሪት ትዕግሥት ታፈረ ቃለ መጠይቅ[43] እና ከተለያዩ የማኅበሩ ኅትመት ውጤቶች ጋራ ለማመሳከር ተሞክሯል፡፡

1. "ለድንግሏ ስል አንገቴን ለሰይፍ እሰጣለሁ!"
2. "ኢትዮጵያ ክርስትና ቀድማ የተቀበለች ቅድስት ሀገር ናት!"
3. "ቅዱስ ገብሬል ተከተለኝ!"
4. "አህዛብ ደጆችሽን አይረግጡም!"
5. "የዓለም ብርሃን ነን"
6. "ጭንቅ ቀርባለችና የሚረዳኝም÷ የለምን ከእኔ አትራቅ" (መዝ 21÷11)
7. "እኔ ከእግዚአብሔር ፊት የምቆም ገብርኤል ነኝ" (ሉቃ 1÷ 19)
8. "ብዙ ውሾች ከበውኛልና የክፉተኞች ጉባኤም ያዙኝ" (መዝ. 22÷ 16)
9. "የታቦት መኖር ከእናንተ ጋር የመኖሬ ምልክት ነው" (ዘጸ. 25÷1)
10. "ሕዝቡን የአምላችሁን የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦትና ሌዋውያን ካህናት ተሸክመውት ባያችሁ ጊዜ ከሰፈራችሁ ተነስታችሁ ተከተሉት" (ኢያ. 3÷3)
11. "እግዚአብሔር ተዋጊ ነው÷ ስሙ እግዚአብሔር ነው" (ዘጸ.15÷3)
12. "የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውን ሁሉ አቅኑ" (ማቴ 3÷3)
13. "ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም" (ዮሐ.3÷5)
14. "መድሐኒዓለም አባቴ ሀገሬን ካጥፊዎች ጠብቃት!"

## አባሪ "መ" (የ2004 ዓ.ም. ጥቅሶች)

እነዚህ ጥቅሶች፡- በአጥኚው ከጥር 7 እስከ ጥር 12 ቀን 2004 ዓ.ም. በጃንሜዳና በዙሪያው ባሉ አካባቢዎች፣ የጥምቀት ክብረ በዓልን ለማክበር ከወጡ የጥምቀት ተመላሾች ከናቲራዎች/ቲሸርቶች እንዲሁም ለየድንኳኖቻቸው እና መድረኮቻቸው ካሠሯቸው (ከሰቀሏቸው) "ባነሮች" ላይ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡

1. ቀ.ነገ. 20÷19 "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል- ገድለህ ወረስኸውን ብለህ ንገረው"
2. መዝ. 17÷ 28 "አንተ መብራቴን ታብራለህና!" ኢትዮጵያ የግዮን መፍለቂያ ቅድስት ሀገር ናት!
3. መዝ. 22÷16 "ብዙ ውሾች ከብበውኛልና የክፉተኞች ጉባኤም ያዙኝ" ድንግል ሆይ!

[43] ቃለ መጠይቁ የተደረገው፣ በማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት ጥር 19 ቀን 2004 ዓ.ም. ነበረ፡፡

4. ዘጸ. 23፥20 "በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆ እኔ መልአኩን በፊትህ እሰዳለሁ"
5. ዘጸ. 15፥3 "እግዚአብሔር ተዋጊ ነው፥ ስሙ እግዚአብሔር ነው"
6. መዝ. 121፥1 "ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ"
7. ራእ. 12፥7 "ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ"
8. ዳን. 12፥1 "ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሳል"
9. ሉቃ. 1፥19 "እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ"
10. ማቴ. 3፥1 "በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በዩሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ"
11. ፩ኛ ነገ. 20፥19 "ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ስፍራ የአንተን ደም ደግሞ ውሾች ይልሱታል ብለህ ንገረው"
12. ማቴ 5፥10 "አሁንስ ምሳር በዛፎች ስር ተቀምጧል፥ እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል"
13. ሉቃ. 1፥44 "እነሆ የሰላምታሽ ድምጽ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማህፀኔ በደስታ ዘሏል"
14. ዘጸ. 25፥1 "የታቦት መኖር ከእናንተ ጋር የመኖሬ ምልክት ነው"
15. ገላ. 3፥27 "በክርስቶስ የተጠመቃችሁ እናንተ ክርስቶስን ለብሳችኋል"
16. ማቴ. 3፥3 "የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውን ሁሉ አቅኑ" እኛ የዓለም ብርሃን ነን!
17. ዮሐ. 3፥5 "ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም"
18. መክ. 12፥1 "የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ"
19. ምሳ. 3፥1 "ልጄ ሆይ ሕጌን አትርሳ፤ ልብህም ትእዛዛቴን ይጠብቅ"
20. መዝ. 21፥27 "የአሕዛብ ነገዶች ሁሉ በፊቱ ይሰግዳሉ" ድንግል ማርያም አማላጃችን ናት!
21. መዝ. 28፥2 "የስሙን ክብር ለእግዚአብሔር አምጡ በቅድስናው ስፍራ ለእ/ር ስገዱ"
22. 2ኛጴጥ.1፥10"ወንድሞች ሆይ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታፀኑ ዘንድ ከፊቱ ይልቅትጉ"
23. ማር.16፥16 "ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል"እኛ የዓለም ብርሃን ነን!
24. ኢያ. 3፥6 "ኢያሱም ካህናቱን የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸከማችሁ በሕዝቡ ፊት እለፉ ብሎ ተናገራቸው"
25. ኢያ. 3፥3 "ሕዝቡን የአምላካችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦትና ሌዋውያን ካህናት ተሸከመውት ባያችሁ ጊዜ ከሰፈራችሁ ተነስታችሁ ተከተሉት"
26. ሚል. 1፥10 "ከፀሀይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአህዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና በየስፍራውም በስሜ ዕጣን ያጥናሉ፥ ንፁህም ቁርባን ያቀርባሉ"
27. ሉቃ. 2፥51 "ከእነርሱም ጋር ወርዶ ወደ ናዝሬት መጣ፤ ይታዘዝላቸውም ነበር፥ እናቱም ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ ትጠብቀው ነበር"
28. ሉቃ. 3፥21 "ሕዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ ቡኋላ እየሱስ ደግሞ ተጠመቀ"
29. መዝ. 21፥20 "ነፍሴን ከሰይፍ አድናት፥ ብቻነቴንም ከወሾች እጅ" አምላኬ ሆይ!
30. 2ኛ ቆሮ. 7፥4 "ስለ እናንተ እምነቴ ታላቅ ነው፤ በእናንተ ምክንያት ትምህርቴ ታላቅ ነው"
31. ሲራ. 34፥9 "ለወገኖቹ በጎ ነገር ያደረገ ማነው እንኳ እናድንቀው"

32. ያዕ. 5÷16 “የፃድቅ ሰው ጸሎትበሥራው እጅግ ሀይል ታደርጋለች”
33. “ሀጢያተኞችን ከፋት ይገድላቸዋል÷ ጻድቃንንም የሚጠሉ ይጸጸታሉ”
34. መዝ. 21÷11 “ጭንቅ ቀርባለችና የሚረዳኝም የለምና ከእኔ አትራቅ”
35. መዝ. 21÷12 “ብዙ በሬዎች ከበቡኝ÷ የሰቡትም ፍሪዳዎች ያዙኝ” ቅድስት ሆይ ድረሺልኝ!
36. 2ኛ ነገ. 23÷7 “በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያሉትን የሰዶማዊያን ቤቶች አፈረሰ”
37. ሲራ. 39÷10 “አህዛብም ጥበቡን ይናገራሉ፤ በሸንጎም መካከል ያመሰግኑታል”
38. መዝ. 67÷1 “እግዚአብሔር ይነሳ: ጠላቶቹም ይበተኑ: የሚጠሉትም ከፊቱ ይሸሹ”
39. ኤር. 23÷14 “ሁሉም እንደ ሰዶም የሚኖሩባትም እንደ ገሞራ ሆኑብኝ” ቅድስት ሆይ!
40. ሲራ. 38÷19 “የደሀ ዘመኑ ሁሉ በብስጭት ሀዘን ያልቃል” ኢትዮጵያ፣ ቅድስቲቱ ሀገር ሆይ!
41. ዘሌ. 20÷13 “ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ፀያፍ ነገር አድርገዋል÷ ፈጽመው ይገደሉ”

**አባሪ “ሠ”**

(መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ የታተመበት የጥምቀት ተመላሾች ቲሸርት ናሙና)

